

በደብረ ሊባኖስ የሚገኘው የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የእጅ መስቀል ።

# ትንሣኤ



"ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእ ናንተ እንሰብካለን" (1 ተሰ. 3 ፥ 9)

የገነተ ጽጌ ቅ ጊዮርጊስ ካህናት ።

ቁጥር 25

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

ማውጫ

አርእስት — ገጽ

ደብዳቤዎች ........ ፩
ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ ለምን ቀሳውስት አይሆኑም? ........ ፪
ፈጽሜ ዳንኩ ........ ፫
መልእክተ ኢትዮጵያ ........ ፭
ምን እንርዳዎ? ........ ፯
ሊቃውንቶቻችን ........ ፰
ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች ........ ፱
የነበረው እንዳልነበረ እንዳይሆን ........ ፲
የሃይማኖት ዐምድ ........ ፲፩
ዜና አብያተ ክርስቲያናት ........ ፲፪
ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ ........ ፲፫
የወጣቶች ዐምድ ........ ፲፬
ክርስቲያናዊ ሕይወት ........ ፲፬
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፲፭
የጤና ዐምድ ........ ፲፯
ይህን ያውቁ ኖሯል? ........ ፲፱
ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ........ ፳
የካህናት ተልእኮ ........ ፳ ፩
የመጽሐፍ ቅዱስ ዐምድ ........ ፳፫
ፊደል ........ ፳፬

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አቀርባለሁ ።

በፈቃዳቸው በውኃ ውስጥ ገብተው በእንጨት ላይ ተንጠልጥለው የሚሞቱ ሰዎች ይገኛሉ ለእንደእነዚህ ያሉ ሰዎች ካህናት ጸሎተ ፍትሐት እንዳይደረግላቸው ያዛሉ ነገር ግን በዚህ ዓይነት ለሞተ ጸሎተ ፍትሐት አይደረግለትም የሚል አንቀጽ ጠቅሶ የሚያስረዳ ካህን አላገኘሁም ፡ እኔም ከመጻሕፍት ውስጥ ይህን የሚያስረዳ ላገኝ አልቻልሁም ስለዚህ ተጨባጭ የሆነውን ማስረጃ በትንሣኤ መጽሔት ቢያወጡት ጠቃሚ ነው እላለሁ ።

ባለም በቀለ ደንበለው
አርሲ ክፍለ ሀገር
ኮፈሌ ከተማ

● ባለም በቀለ ደንበለው ለጥያቄዎ መልስ ለማግኘት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስን ጠይቀናል ፡ ብፁዕነታቸውም የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል ። ሥርዐተ ቤ/ክርስቲያን የሚፈጽምላቸው በሥርዐተ ቤ. ክርስቲያን ለኖሩ ነው ፡ ራስን በራስ መግደል በክርስትና እምነት ዘንድ ፍጹም ኃጢአት ነው ። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ትላለች "ለቀታሌ ነፍሱ አልቦቱ ሕይወት ፡ ራሱን የገደለ ሕይወት የለውም" ከዚያም በፊት "ኢትግበር እኩየ ዲበ ነፍስከ በራስህ ላይ ክፉ አታድርግ" ብላ ታስተምራለች ። ባጠቃላይ በፈቃዳቸው በእንጨት ተንጠልጥለው በባሕር ጠልቀው ሽጉጥ ጠጥተው የሚሞቱ ሁሉ ክርስቲያኖች ናቸው ማለት አንችልም ። ክርስቲያን ይህን አያደርግምና ። ስለዚህ እንደእነዚህ ላሉት ሁሉ ሥርዓተ ፍትሐት እንዳይፈጸም ቤ. ክርስቲያናችን ወስናለች ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ይድረሳችሁ እያልሁ ሰላምታ አቀርባለሁ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በወሎ ክፍለ ሀገር በግሼን እንዳለ ይነገራል ሙሉ መስቀሉ መጥቷል ? ወይስ ከፊሉ? ከሆነስ ሌላው ክፍል በየትኛው ክፍለ ዓለም ይገኛል ?

መምህር ገብረ መድኅን በየነ
አዲስ አበባ

● መምህር ገ/መድኅን ስለ ጥያቄዎ እናመሰግንዎታለን ፡ ወደ ሀገራችን የመጣው ግማደ መስቀሉ እንጂ ሙሉ መስቀሉ አይደለም ። የመጣውም ግማደ መስቀል ራስዎ እንደገለጡት በወሎ ክ/ሀገር በግሼን ይገኛል ። ሌላው ግማድ ደግሞ በኢየሩሳሌም እንደሚገኝ ይነገራል ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ሰኔ 12 ቀን 1971 ዓ.ም. በየካ ቅ/ሚካኤል ቤ. ክርስቲያን ከጡዋቱ በአንድ ሰዓት ደርሼ ጸሎት በማድረስ ሳለሁ በ5 ሰዓት ታቦቱ ወጥቶ 3 ጊዜ ዑደት ከተደረገ በኋላ የመዘምራንና የመንፈሳውያን ወጣቶች መዝሙር ተሰምቶ መንፈሳዊ ስብከት በሚደረግበት ጊዜ ታቦቱን የተሸከመው ቄስና ምእመናን ቆመው ስብከት በሚሰጥበት ጊዜ ብፁዓን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወንበር ቀረበላቸውና ስብከቱ እስከሚያልቅ ተቀመጡ ፡ ይህን በማየቴ በጣም አዘንኩ ፡ ይህ ድርጊት መፈጸሙ ሥርዐት ማሻሻላቸው ነው? ወይስ እነሱ ከምእመናን በላይ መሆናቸውን ለማሳወቅ ያደረጉት ነው? ምክንያቱ ስላልገባኝ ቢገልጡልኝ አመሰግናለሁ ።

ቅሬታ ከተሰማን ምእመናን አንድዋ
ቅድስት አማረ አዲስ አበባ

● ቅድስት አማረ በቅድሚያ ስለጻፉልን ደብዳቤ ምስጋናችንን እናቀርባለን፤ ለጥያቄዎ ትክክለኛ መልስ ለማግኘት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስን ጠይቀናል ብፁዕነታቸውም የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል ።

የደከመ ተቀምጦ የበረታም ቆሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰማ ቤተ ክርስቲያናችን ትፈቅዳለች ፡ ሰኔ 12 ቀን እርስዎ ባስቀደሱበት ቤ. ክርስቲያን ምእመናንና ታቦቱን የያዘው ቄስ ቆመው ሳሉ የተቀመጡት አባቶች ደክሞአቸው ይሆናል እንጂ ጳጳሳት ይቀመጡ ምእመናን ይቁሙ የሚል ሥርዓት በቤ/ክርስቲያን የለም ፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል ከቻሉ ሁሉም ቢቆሙ መልካም ነው ፡ ካልቻሉ ግን ጸሎቱን አቋርጦ ከመሄድ ተቀምጠው ትምህርቱን አዳምጠው ቢሄዱ የተሻለ ነው ሲሉ ብፁዕነታቸው ገልጠውልናል ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ትንሣኤ መጽሔት በዝግጅቱ በጣም አስደሳች መንፈሳዊ መጽሔት እንደሆነ ስናገር የተሳሳትሁ አይመስለኝም ። ምክንያቱም ጊዜውን እየተከተለ ማለት በዓለ ትንሣኤን በዓለ ዕርገትንና ጰራቅሊጦስን እንዲሁም የቅዱሳን ሰማዕታትንና መላእክትን መታሰቢያ እያመለከተ የሚያቀርባቸው ዝግጅቶች እጅግ በጣም ያስደሰቱኝ መሆኑን ለመጽሔቱ አዘጋጅ ስገልጥ ከፍ ያለ ደስታ እየተሰማኝ ነው ግን መጽሔቱ በምን ወርና ዓመተ ምሕረት እንደ ታተመ ስለማይገልጥ ይታሰብበት እላለሁ ።

የመጽሔቱ ደንበኛ
መኰንን ተረፈ
ከሰበታ ከተማ የመንገድ ሥራ ባለሥልጣን
ባልደረባ ሾፌር

● አቶ መኰንን ተረፈ ስለ መልካም አስተያየትዎ እጅግ እናመሰግንዎታለን ። እርስዎና ሌሎችም ደንበኞቻችን በሰጡን አስተያየት መሠረት እነሆ ከመስከረም ወር 1972 ዓ.ም. ጀምሮ ወሩንና ዓመተ ምሕረቱን መጥቀስ ጀምረናል ወደፊትም አስተያየትዎን አይንፈጉን ።

***

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 23 በወጣው እትም ላይ ወ ት ትበርህ ኮከብ ከደሴ ፡- ልብሰ ተክህኖ ለብሶ 29818 አ.አ. የሆነች መኪና ሲያሽከረክር ያየችውን ዲያቆን አድራሻና ታሪክ ጠይቃን ነበር ። መልሱን ራሱ ስለላከልን እነሆ በዚህ እትማችን ፎቶግራፉንና የሕይወት ታሪኩን ባጭሩ አውጥተነዋል ።

ወደ ገጽ [፲፫]ል



www.ethiopianorthodox.org

## ርዕሰ አንቀጽ

# ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ ለምን ቀሳውስት አይሆኑም ?

በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተማሩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብዙ ናቸው ባይባልም በመጠኑ አሉ ፤ ይሁን እንጂ ትምህርታቸውና አላማው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሁኖ ሳለ ቅስና ተቀብለው በቅስናው ሙያ የተሰማሩ የሉም ፤ አንዳንዶቹ ቅስናውን ቢቀበሉትም በማጥመቅ ፤ ቀድሶ በማቁረብና ፤ በማስተማር በጠቅላላ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም በሥራ አይገልጡትም ፡ አብዛኛዎቹ ደግሞ ከነአካቴውም ቅስና መቀበሉን ትተው በሌላ ስም እየተጠሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመሆን ይፈልጋሉ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን መቀበል ተቀብሎም በሥራ መተርጐም አለበት ።

በአገር ውስጥ ተምረው የአቋቋም ፤ የዜማ ፤ የመጻሕፍትና የቅኔ መምህራን የሆኑ ሁሉ የቅስናን ሙያ እንደ ዝቅተኛ ሙያ ይመለከቱታል ፤ በቅስና የሚያገለግለውንም ካህን "ሰሞነኛ" የሚል የንቀት ቅጽል ይሰጡታል ፤ ብዙዎቹ መምህራን ራሳቸው የቅስናን ሙያ ዝቅ አድርገው ከማግታቸውና እነርሱም በቅስና ሙያ ቢያገለግሉ ክብራቸው የተዋረደ ስለሚመስላቸው ተማሪዎቻቸው እንዳይቀድሱ ይከለክላሉ ፤ የዲቁናንና የቅስናን ሙያ ያጥላሉ ። ግን የአድባራት አስተዳዳሪዎች ሆነው የበላይነቱን ለመያዝ ይጥራሉ ፤ ተምረው ከተገኙ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ለምን ይሆናሉ? አንልም ፤ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የምእመናን መሪ መሆን ያለበት ቄስ ነው ፤ ቄስ መሆን የሚገባውም የተማረ ፡ ለሚጠየቀው ጥያቄ መልስ መስጠት የሚችል ፤ በትምህርቱ የምእመናንን ሥጋዊና መንፈሳዊ አቅዋም የሚያስተካክል ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ የተረዳ መሆን እንዳለበት ለመጠቆም ነው ።

ወደ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ተልከው ነገረ መለኮትን ተምረው የተመለሱ ሊቃውንትም በቢሮ ተቀምጠው የነገር (የሙግት) ዶሴ ሲያገላብጡ ዕድሜያቸውን ከሚያሳልፉት ይልቅ በቅስና ሙያና በሥነ ጽሑፍ ዓለም ቢሠማሩ ኀብረቱ ሰቡን በበለጠ እንደሚጠቅሙ አያጠራጥርም ። ትምህርታቸውም የሥነ ጽሑፍና የቅስና ትምህርት ለመሆኑ አያጠያይቅም ። ለቅስናው ሙያ ከፍተኛ ትምህርት የማያስፈልገው የሚመስላቸው ይኖሩ ይሆን ? ስለዚሁ የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ እንዲህ ይላል "ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲስ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት አምላካውያት ሠናያት ወፈድፋደሰ አርባዕተ ወንጌላተ ፡ መልካም የሆነ የአምላክን ነገር የሚናገሩ መጻሕፍትን ፤ ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያላወቀ አንዱ እንኳን ቄስ አይሁን" (ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 6፣ 212) የቤተ ክርስቲያንዋ መመሪያ ይህ ሆኖ ሳለ ብዙዎቹ ቀሳውስት ያነበቡትን ወንጌል አብራርተው ለሕዝብ የማያስተምሩ ሆነው ይታያሉ ።

ታዲያ ነገረ መለኮትን አብራርተው የማስረዳት ፤ መጻሕፍትን ተርጉመው የማስተማር ችሎታ ያላቸው ሊቃውንት ለምን ቀሳውስት ሆነው መሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም አያገለግሉም? ምን አልባት በቅስና ዓለም ቢሰማሩ በቢሮ እየሠሩ የሚከፈላቸውን ደመወዝ ለማግኘት አይችሉ ይሆን ? ወይስ ለባለዲግሪው ካህን ፤ አስተምሮ ማጥመቅ ፤ ቀድሶ ማቁረብና ወንጌልን ማስተማር ዝቅተኛ ሥራ ይመስለው ይሆን ? ተመልካቾች ምን ይላሉ ፤ እኛ ግን ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ ሁሉ በቅስና ሥራ ተሠማርተው ምእመናንን ቢያደራጁና ቤተ ክርስቲያንን ቢያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን ርምጃ የተቃና እንደሚሆን አንጠራጠርም ።

## ፈጽሜ ዳንኩ

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 21 ከ 1964 ዓ.ም. እስከ 1968 ዓ.ም. ድረስ አቶ ፈቃዱ ወልደ ማርያም ስንኩል ሆነው በብርኩማ እየተንፏቀቁ ፈጽሞ ድውይ በመሆን ከቀዩ በኋላ በጥር ወር 68 ዓ.ም. ከበሽታቸው መፈወሳቸውን በመግለጽ እኒህን ሰው ከነፎቶግራፋቸው አትመን ማውጣታችን ይታወሳል ። እኒህ ሰው በ1964 ዓ.ም. በድንገተኛ ተለክፈው ሀገረ ሕይወት ሆስፒታል ዘጠኝ ወር ተኩል በሕክምና ሲረዱ



ሽባና ዲዳ የነበሩት አቶ ፈቃደ ወ ማርያም ፈጽመው ዳኑ

ቆይተው ሥቃዩ ተቀንሶላቸው ሺባ ሆነው ከሆስፒታል ይወጣሉ ፤ ከዚያም ከሺባነት በሽታቸው ለመዳን ወሲሶ አባ ወልደ ትንሣኤ ግዛው ዘንድ እንደሄዱ በዚያው እየተጠመቁ ሳለ እምቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መላእክትን አስከትላ ልጇዋን ይዛ ሄዳ ሌሊት በራዕይ ትገለጥላቸውና የምትፈወሰው እዚህ ሳይሆን አምቦ ሀገረ ሕይወት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ስለሆነ በዚያ ሄደህ ንስሐ ግባና እዚያ ለምነኝ ብላቸው ትሠወራለች ።

እርሳቸውም በዚሁ በእመቤታችን ቃል መሠረት ወደሀገረ ሕይወት ኪዳነ ምህረት ሄደው በዚያ እንዳሉ በቃል ኪዳኑዋ መሠረት ሌሊት በራዕይ ተገልጻ ከልጅዋ ጋር ሆና ሰውየን ቀስቅሳ ሰውየውን እንደፈወሰችው በጊዜው ታሪኩን አብራርተን ማውጣታችንን እናስታውሳለን ።

ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜ መሳው ሰውነታቸው ሲፍታታና ሲፈወስ አንደበታቸው ሳይፈወስ በመቅረቱ የእግዚአብሔርን መሐሪነት ለመመስከር እንዲችሉ አንደበታቸው ባስመፈታቱ ቅሬታቸውን በጽሑፍ ገልጸው ፤ እመቤታችን ግን "የእኔን አማላጅነት ፤ የልጄን መሐሪነት ፤ ንገር መስክር አንደበትህ ይፈታልሀል እንዳለቻቸው መግለጣቸውን በጊዜው መጻፋችን ይታወሳል ።

ስለሆነም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በገባችላቸው ቃል ኪዳን መሠረት አቶ ፈቃደ ወልደ ማርያም ምላሳቸው ተፈቶ እንደበታቸው መናገር ችሎ የእግዚአብሔርን ረዳትነት ፤ ፈዋሺነት መሐሪነትና ይቅር ባይነት የእመቤታችንን አማላጅነት ሲመሰክሩ አገኘናቸው ።

ይህ የሆነው ነሐሴ 24 ቀን 1971 ዓም. የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዓመታዊ በዓል በተከበረበት ወቅት አዲስ አበባ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ነው በዚሁ ዕለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት መምህራን ለማስተማር ወደ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ሄደው ስለነበረ በዚያው ዕለት ነው ።

አቶ ፈቃደ ወልደ ማርያም ወደ ድርጅቱ መኪና ጠጋ ብለው መጽሔት አለ? ሲሉ ጠየቁን እኛም አለ አልናቸው ። እርሳቸውም የእርሳቸው ፎቶግራፍ ያለበትን ቁጥር 21 ትንሣኤ መጽሔት አውጥተው ፎቶግራፋቸውን እያሳዩን «የዚህ ዓይነት አለ» አሉን። እኛም በመጠራጠር እያተመለከትናቸው ሳለ ይኸ እኮ እኔ ነኝ አሉን ።

እኛም ታዲያ ጽሑፉ በተጻፈበት ጊዜ እንደበቱ ድዳ ነው ። መናገር አልችልም ብለውን ነበር ።

ዛሬ እንዴት መናገር ቻሉ ? አልናቸው እርሳቸውም «እመቤታችን በገባችልኝ ቃል ኪዳን መሠረት መናገር ቻልኩ የምሥራች!» አሉን ።

አሁን በሚገባ ድነዋል ? ብለን ብንጠይቃቸው ፈጽሞ ዳንኩ አሉን ።

ተስፋ ጥሩነህ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ዲያቆን ኃይሌ አየለ በወሎ ክፍለ ሀገር በሳይንት በተድባበ ማርያም ተወለደ ፤



ዲያቆን ኃይሌ አየለ ይህ ነው

በዚሁ ደብር ከመናኝ ገ መድኅንና ከመምህር ጌራ ወርቅ ፀምሩ የቤ ክርስቲያን ትምህርት ተማረ። በአዲስ አበባ መካነ ሕይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤ ክርስቲያን ለ7 ዓመታት በዲቁና አገልግሎአል ። በዚህም ጊዜ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሎአል ። አሁንም በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤ ክርስቲያን በዲቁናና በሾፌርነት ይሠራል ፡- አድራሻውም የሚከተለው ነው ።

የመልእክት ሣጥን ቁ. 2804

ስልክ ቁ. 11-86-52

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሰበካ ጉባኤ በሚቋቋምበት ወቅት ቅስቀሳ ሲደረግ ማናቸውም ምእመን የዓመቱን ክፍያ ከፍሎ መታወቂያውን ከያዘ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ወይም ክፍለ ሀገር ሂዶ የሞት አደጋ ቢደርስበት





www.ethiopianorthodox.org

በቤተሰቡም ሆነ እርሱ በሚያስተዳድራቸው ሁሉ ነፃ አገልግሎት ያለአንዳች ክፍያ ያገኛል የሚል ነበር ።

አሁን ግን እንኳን ነፃ አገልግሎት ይቅርና ከቶውንም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአንዱ ቤተ ክርስቲያን የከፈለበትን መታወቂያ ቢያሳይ የከፈልክበት ሌላ ቦታ ነውና አንቀበልም እያሉ ደግሞ በዚህ ላይ እናስቀብርም አለበለዚያ 25 ብር ለመቃብር ክፈሉ እያሉ ሰውን ያጉላላሉ ይህ ከሆነ ሰበካ ጉባኤው ላለበት ደብር እንጂ ለሌላ ደብር የማያገለግል ከሆነ ጥቅሙ ከምን ላይ ነው? ከሰበካ ውስጥ ከክፍያ ነፃ መሆን ብቻ ነው፤ ስለዚህ የፌተኛው ቅስቀሳ ለምን ከሥራ ላይ አልዋለም ለወደፊቱም ይህ ካልተሻሻለ ብዙዎች ምእመናንን ወደቅሬታ አይስብም ? ትንሣኤ መጽሔት ምን አስተያየት እንዳለው እንዲያብራራልኝ በተስፋ እጠባበቃለሁ ።

ጥሁመልሳን ከበደ

ከአዲስ አበባ

● የቀረበውን ጥያቄ ተመልክተነዋል የዓመቱን የሰበካ ጉባኤ አባልነት ክፍያ የከፈለ ምእመን ነፃ አገልግሎት ያለ አንዳች ክፍያ ያገኛል ። ይሁን እንጂ በአንድ አካባቢ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት አንደኛው የመቃብር ቦታ ሲኖረው ሌላው አይኖረውም ። የመቃብር ቦታ በሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት በተመዘገቡ ምእመናን ችግር ተፈጥሮ ስለነበረ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሰብሳቢነት የተመራው ጉባዔ ሰኔ 11 ቀን 1971 ዓ.ም. የሚከተለውን ወስኖአል ።

“የመቃብር ቦታ በሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የሚገኙ የመቃብር ቦታ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለመቃብሩ ቦታ ጽዳትና ለጥበቃው አገልግሎት የሚያስፈልገውን ክፍያ በየሰበካ ጉባኤያቸው አጥንተውና ተስማምተው በመወሰን እንዲከፍሉ ሆኖ በሰበካ ጉባኤ የተመዘገበና አስተዋጽኦውን በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የከፈለ ምእመን ሲሞት ጸሎተ ፍትሐቱ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞ አስከሬኑ የመቃብር ቦታ ወደ አለበት ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ ዋጋ ሳይጠየቅ በነፃ እንዲቀበር”

ይህ ውሳኔ ለጥያቄዎ ትክክለኛ መልስ ይሆናል ብለን እናምናለን የሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም ቅስቀሳ ሲደረግ የተነገረውንም ቃል ውሳኔው በሥራ ላይ እንዲውል አድርጎታል ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

አንድ ያልገባኝ ነገር አለ የመነኩሴ ሰው ይህን ዓለም በመናቅ በአንድ በተወሰነ ገዳም በመኖር ስለ ሀገር ሰላም ስለ ሕዝብ ደኅንነት መጸለይ ሲገባው በአሁኑ ወቅት የሚታዩ መነኮሳት መንፈሳዊ ተግባራቸውን ወደኋላ ጥለው የዕለት ጥቅማቸውን በማግበስበስ ላይ ይገኛሉ ። ለሌላው ስጡ ለገሱ እያሉ ይሰብካሉ እነሱ ግን አንድም ነገር ሲሰጡ አናይም ስለእነዚህ መነኮሳት ትንሣኤ ምን አስተያየት አለው ?

ወ እማኑኤል ዘለለው

አዲስ አበባ

● መነኩሴ ሞተ ማለት ነው ፤ ሞተ ማለትም ተለየ ማለት ነው። ስለዚህ መነኩሴ ሲባል የሚገባው 1ኛ ገንዘብን ፈቃደሥጋንና የዓለምን ምኞት ሁሉ ንቆ የተወ፡ 2ኛ በገዳም የሚኖር የላመ የጣመ የማይቀምስ ወይባና ማቅ የሚለብስ ፤ 3ኛ ለዘለዓለሙ ሥጋ መብላትን የተወ ፤ የሚያሰክር መጠጥን የማይጠጣ ለቁመተ ሥጋ ያህል ብቻ እየተመገበ የቅንጦቱን ሁሉ የቀነሰ መሆን እንዳለበት በፍ ነገ አንቀጽ 10፣357 - 360 ተገልጾአል ።

ጠያቂው እንደተመለከቱአቸው ከተማ ለከተማ እየዞሩ ገንዘብ የሚያግበሰብሱና ጠጅ የሚቸልሱ ግን መነኮሳት አይደሉም ስለ እነርሱስ መጽሐፉ ‘‘ዘጕየ እምአጸባ’’ ከችግር የተነሣ የኮበለለ ጥሮ ግሮ ራሱን ማስተዳደር ያቃተው በማታለልና በልመና ኑሮውን ለመግፋት የፈለገ ሰነፍ ነው ይላል ።

ቤተ ክርስቲያን እናሳድሳለን ገንዘብ ጣሉልን የሚሉት መነኮሳትና ባሕታውያን መሰሎች ሁሉ የሚሰበስቡትን ገንዘብ ለራሳቸው መጠጫ እንጂ በለፈለፉት መሠረት ለቤተ ክርስቲያን እድሳት የማያውሉት መሆኑን ምእመናን ሁሉ እንዲገነዘቡት በዚህ አጋጣሚ እናሳስባለን ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ሰላም ከናንተ ጋር ይሁን ።

በቁጥር 22 የሐምሌ ወር ትንሣኤ መጽሔት ላይ ተማሪ ክፍሉ ደምሴ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ቁርባን መለያየት ለጠየቃችሁ ጥያቄ የሰጣችሁት መልስ ግልጽ ስላልሆነልኝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

ሥጋ ወደሙ በዓለም በግልጽ ቢፈተት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና እምነቷ ከነሱ የሚለያዩ እስከሆነ ድረስ እንዴት በግልጽ ይሁን ልትሉ ቻላችሁ በተመልካቾችስ ዘንድ ሌላ ትችት ሊያመጣ አይችልም ወይ ?

ምኒልክ ካሣ ከመካነ ሕይወት ገ

መንፈስ ቅዱስ ወጣቶች

● ምኒልክ ካሣ ለተማሪ ክፍሉ ደምሴ የተሰጠው መልስ ግልጽ አልሆነልኝም አልክ እንጂ በጥያቄህ ነገሩ እንደገባህ ይታወቃል ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ቢሆንም ሥጋውደሙ በግልጥ ቢፈተት እምነትን ማፋለስ አይሆንም ከዚህም ሌላ ከእኛ ጋር በእምነትና በሥርዓት አንድ የሚሆኑት የአርመን የሕንድ የእስክንድርያና የሶርያ አብያተ ክርስቲያናት ሥጋውን ደሙን የሚፈትቱት በግልጥ ነው ፤ በግልጽ መፈተቱም ምንም አይነት ትችት የሚያመጣ አይመስለንም ፤ የሚተቹ ቢኖሩም ምሥጢረ ቁርባን “ምሥጢር” መባሉ እንዴት እንደሆነ ያልተረዱ መሆን አለባቸው ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

እኔ ብዙ ትምህርት የሌለኝ ቤተ ክርስቲያን የማፈቅር ነኝ ። ግን ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲጣሉ እያየሁ ወደ ቤ ክርስቲያን ለመሄድ ቅር ተሰኝቻለሁ ። ለምሳሌ የካቲት 28 ቀን 1971 ዓ.ም. በአማኑኤል ቤ ክርስቲያን ምእመናን በተሰበሰቡበት ሁለት ቀሳውስት በዱላ እስከ መደባደብ ሲጣሉ አይቻለሁ ። 2ኛ ሚያዝያ 7 ቀን እሑድ 1971 ዓ.ም. ሁለት ቄሶች በከባድ ጥላቻ ሲጣሉ ተመለከትሁ ። አንደኛው በየካቲት 28 ቀን ጠብ ያሜሩት ቄስ ናቸው ። 3ኛ 16

ወደ ገጽ ፤ ዞሯል



# መልእክተ ኢትዮጵያ

ቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን

ከራሺያ



የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች
ምክሬን ተቀበሉ የኢትዮጵያ ልጆች ።
እናታችሁ እኔ ውቢት ኢትዮጵያ
የታሪክ እመቤት የዕውቀት ባለሙያ ፤
ትርንጎ ብርቱካን የማፈራላችሁ
የሰጣችሁኝን የምቀበላችሁ
መሬቴ ለምለሙ የዘራችሁትን የሚያበቅልላችሁ
ስንዴ ጤፍ ማሽላ የእህልን አይነት ሁሉ የማመ
ርትላችሁ ፤
ማር ቅቤ ወተቱን የማፈስላችሁ
ሙክት ፍሪዳውን የማሰባላችሁ
የጤንነት አየር የማነፍስላችሁ
ወንዙ ወንዛ ወንዙ ደኑ ዱራዱሩ
ኸረቱ በረሃው ጋራው ሸንተረሩ
ምድሬን ለመጎብኘት እኔን ለማየት
ብዙ የሚመኘው የዓለም ቱሪስት
እኔ ኢትዮጵያ ወላጅ እናታችሁ
ያለብኝን ችግር ስሙኝ ልንገራችሁ ።
እጅግ የበደለኝ የተጐዳሁት
ራብ ድንቁርና የፊውዳል ሥርዓት
ለሚመለከተው ላጤነው አስተውሎ
የልቤ ረመጡ ያንጀቴ ቃጠሎ
ድህነት በሽታ ራብ ድንቁርና
ከሰው ኋላ መቅረት ኑሮ ከንቱ መና ።
ያለፈው አለፈ አይጠቅምም ጸጸት ፤
ሲያፈስ ለኖረ ላለፈው ክረምት
ጣሪያ አይከደንም አይሠራም ቤት
ለዚህ መድኃኒቱ ታላቁ አብነት ፤
ዛሬ በትግላችን በወሳኙ ወቅት
መማር መመራመር ጠንክሮ መሥራት
ሕፃን ሽማግሌ ሳይባል ሴት ወንድ
ማለዳ ይነሳ ለሥራ ሳይረፍድ
ድንቁርና ይጥፋ ጨለማው ይለፍ
ለፊደል ዘመቻ ሁሉም ይሰለፍ
በኅብረት ይቀደድ ጥቁሩ መጋረጃ
ወደፊት ይፋጠን የትምህርቱ ርምጃ
ሕፃናትም በርቱ ፊደልን ቁጠሩ
እንብቡ ተርጉሙ ጥበብን ፍጠሩ
ትምህርት ዕውቀት በሉ ጮሁ ተናገሩ
ኢትዮጵያ ቅደሚን በኅብረት ዘምሩ
ድንቁርና ይውደም ይሰደድ ከገሩ
ተማሩ ልጆቼ በርቱና ተማሩ
ለጥበብ ታገሉ በውቀት ተጣጣሩ
የትምህርት አዝመራ መሰብሰቢያው ወቅቱ
ልጅነት ነውና ሳትሰለቹ በርቱ ።
ልጆቼ ተማሩ በርቱና ተማሩ
ለጥበብ ታገሉ ለውቀት ተጣጣሩ ።
ለነገ አትበሉ ነገን ነገ ያውቃል ፤
ዕድሜ ገለባ ነው ተንሸራቶ ያልቃል ፤
ካለፈ በኋላ ልጅነት በከንቱ
ለማንም ለምንም አይጠቅምም ጸጸቱ
ካለፈ በኋላ ጊዜውና ወቅቱ
ዋ ተምሬ ቢሆን ቀረብኝ ማለቱ
ራስን መጉዳት ነው ትርፉ ብስጭቱ ።
ልጆቼ ተማሩ በርቱና ተማሩ
ለጥበብ ታገሉ ለውቀት ተጣጣሩ ።
የጥበብ ጉዳና ሩቅ ነው ሀገሩ
ጉዞውን በጊዜ ታጥቃችሁ ጀምሩ
ማቄን ጨርቄን ማለት ምክንያት መፍጠሩ
ለጉበዝ ተማሪ ውርደቱ ነው ነውሩ ።
ተማሩ ልጆቼ በርቱና ተማሩ
ለጥበብ ታገሉ ለውቀት ተጣጣሩ ።
ራብ ድንቁርና ድህነት በሽታ
በተማረ ሰው ዘንድ አያገኙም ቦታ
ያልተማረ ፍጡር ሸክም ነው ለሁሉ
ይህን ተረድታችሁ በርቱና ታገሉ ።
ኑሮን ለመቋቋም በጥበብ ታጠቁ
ማለዳ ተነሱ ለትምህርት ንቁ
መና ከደመና እንዳትጠብቁ ።
ተማሩ ልጆቼ በርቱና ተማሩ
ለጥበብ ታገሉ ለዕውቀት ተጣጣሩ
የኑሮ ቅያሱ ይኸው ነው መሥመሩ ።
ሃይቆችን በጀልባ ፤ ባህሩን በመርከብ የሚሸ
ጋገሩ
የብሱን በመኪና የሚሽከረከሩ
ባውሮፕላን ባየር መጥቀው የሚበሩ
ሬዲዮ ፤ ቲቪ ፤ ሌላ ሌላውንም ሌላውንም ሁሉ
ሌት ከቀን በመሥራት ደከመኝ ሳይሉ
በመልክ በመልኩ እያቀናበሩ
ሠርተው ያቀረቡ ዛሬም የሚሠሩ
በውቀት የበሰሉ ጠልቀው የተማሩ
የፍጥረትን ባህርይ የተመራመሩ
ባለሙያዎች የሰው ልጆች ናቸው
መላእክት አይደሉም ፤ ከሰማይ አልመጡም
ሰው ነው ተፈጥሮአቸው
በቴክኖሎጂ ዕውቀት ስለተራቀቁ
ይህን ሁሉ ጥበብ ለመፈልሰፍ በቁ ።
ታዲያኮ ልጆቼ በርቱና ተማሩ
ለጥበብ ታገሉ ለውቀት ተጣጣሩ ።
እንጃልሽ አላውቅም እንቺ እማየ ኋላ
እኔ ዛሬ ቁርሴን ምሳየን ሳልበላ
ሱሪየ ተቀዶ ሜማው ተገንጥሎ
እግሬን እየፈጀው ያስፋልቱ ቃጠሎ
እርሳሴ ተሰብሮ እስክሪፕቶው ቀልጦ
ኳስ ሜዳ ወድቄ ጉልበቴ ተልጦ ።
ደብተር ተገንጥሎ መጻፊ ተቀዶ
ሜዳው ገደል ሆና ገደሉ ተንዶ
የሚለው ሐተታ የሰነፍ ልጅ ባህሪ
አያስፈልገውም ፤ ስሜት አይሰጠውም ለጉበዝ
ተማሪ
ያገኙትን ለብሶ በመጠኑ በልቶ
ችግርን በትምህርት ለመጣል ጉጉቶ
መማር መመራመር መታገል ነው ተግቶ ።
ስላለፈው ጊዜ ተረት ስናወራ ፤
ዛሬ አይለፍብን የራሳችን ተራ ።
ማልደን እንነሳ ጠንክረን እንስራ ።
በትግላችን ይጥፋ ራብ ድንቁርና
በቦታው ይስፋፋ ልማት ብልጽግና
በብርሃን ጊዜአችን እንመላለስ
ሰው ከደረሰበት ደረጃ እስክንደርስ
ምኞት አይመረን እንቅልፍ ይቀነስ ።
ጉዞአችን ረጅም መራራ ነው ትግሉ
በወሬ አይወጣም ስርጡና ገደሉ ።
ቆራጥ አብዮተኛ ለትግሉ ይቆርጣል
የመራራም ትግል ፍሬው ይጣፍጣል ።
ሬት ነው ትግላችን ጉምዛዛ መራራ
ቆራጥ ይጠይቃል ሃሞተ ኮስታራ
ጉበዝ! ወሳኝ ታጋይ መንፈሰ ጠንካራ ።
ተባብረን እንስራ እንባባል ኳዴ
ለምለሟ ኢትዮጵያ ትልበስ አረንጓዴ ፤
በዳቦ ይሞላ የዳቦ ቅርጫቱ ።
ያለፈው ይበቃል ችግሩ ብሶቱ
ይልበስ ይጐናጸፍ የታረዘ ገላ
የቸገረው ያግኝ የተራበው ይብላ
ሞሰቡ አይራቆት ሰሚታችን ይሙላ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፡ ለችግራቸው
መፍትሔ የሚሰጡበት ፡ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ
ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቊጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


በአሁኑ አምዳችን ከብዙ ጊዜ ስቃይና
መከራ በኋላ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳ
ነ ምህረት ጠበል ፈውስ ያገኙትን ሕሙ
ማን ነሐሴ 16 ቀን 1971 ዓ.ም የኪዳነ
ምሕረት ዓመታዊ በዓል በተከበረበት
ዕለት በቦታው ተገኝተን ያነጋገርናቸ
ውን ሰዎች የስም ዝርዝርና የበሽታው
ን ዓይነት እንዲሁም እንዴት ፈውስ
እንዳገኙ አቅርበናል ።

### 1 ገነት አበጀ

ወላጅ አባትዋ አቶ አበጀ ተሰማ እን
ዲህ በማለት አስረድተውናል። ልጄ
ገነት አበጀ በሰኔ ወር 71 ዓ.ም እጅግ
በጣም ታማ ሊሻላት ባለመቻሉ ታስራ
ወደ ኪዳነምህረት አመጣሁዋት በመጣ
ች በሰባተኛው ቀን ድና በፈቃድዋ ያለ
ምንም ርዳታ ወደኪዳነ ምህረት ቤተ
ክርስትያን ሄደች። እንደገና ከአምስት
ቀኖች በኋላ በሽታው ስለተነሳባት በዚ
ሁ ጠበል እየተጠመቀች ተአምረ ማር
ያም እየተነበበ በመስቀሉ ስትታሽ ከቆ
የች በኋላ አሁን እንደምታዩአት ፈጽማ
ድናለች ብለውናል ።

### 2 ሞገስ ገብረ ጻድቅ

ከሚያዝያ ወር 71 ዓ.ም ጀምሮ በ
ሽታው ከምን እንደያዘኝ ሳላውቀው እ
ያስጮኸ የትም ወደአገኘሁት ቦታ ሁሉ
በርሬ እንድጠፋ ያደርገኝ ነበር። በዚህ
ም ምክንያት ብዙ ጊዜ ወደ በርሃ ጠፍ
ቴ ሄጄ ነበር።

በሚያዝያ ወር መጨረሻ ወደዚሁ
ኪዳነ ምህረት መጥቼ ጠበል ስጠመቅ
ቆይቼ ልክ በአሥራ አምስት ቀኔ ከያዘ
ኝ በሽታ ልፈወስ ችያለሁ በማለት በደ
ስታ እየፈነደቁ ከእልልታ ጋር ገልጸው
ልናል ።

ከሆዴም እንደ እባብና እንደ እንቁ
ላል የመሳሰሉ ነገሮች በብዛት ወጥተ
ውልኛል ብለዋል ።

### 3 ግርማ ኪሮስ

በየካቲት ወር 71 ዓ.ም ታምሜ ቀኝ
እግሬ ሽባ ሆኖ ነበር። ወደዚሁ ወደ ኪ
ዳነምህረት ቤተ ክርስቲያን መጥቼ ጠ
በል እየተጠመቅሁና እየጠጣሁ አሥ
ራ አምስት ቀኖች እንደቆየሁ በአስራ
አምስት ቀኔ ሺባ የሆነው እግሬ ድኖል
ኝ በእግሬ ቆሜ ለመሄድ በቃሁ ብለዋ
ል።

### 4 አድማሱ ሞላ

በመኪና ከባድ ግጭት ደርሶብኝ ራ
ሴ በከባድ ሁኔታ ተመታ። ወደልዩ ል
ዩ መድኃኒት አዋቂዎች ናቸው ወደሚ
ባሉ ሰዎች እየሄድሁ የሀገር መድኃኒት
ባደርግም እንዲያውም ብሶብኝ አእም
ሮዬ ተነካና አእምሮዬን ስቼ አበድሁ
ወዲያው ቤተሰቦቼ እጅና እግሬን አስ
ረው እዚሁ አመጡኝ። እዚሁ ጠበል ጥ
ቂት ቀኖች እንደተጠመቅሁ ሕይወቴ
ን ማወቅ ችያለሁ።

አሁን የመጀመሪያው ጤንነቴ ተመል
ሶልኝ በመልካም ጤንነት ላይ እገኛለ
ሁ ሲሉ የደስታ ፈገግታ ፈገግ ብለው
ነግረውናል።

### 5 አያሌው በላይነህ

በ1970 ዓ.ም ባልታወቀ ምክንያት
ሁለቱ እግሮቼ ሺባ ሆኑ፣ አራት ወሮች
በስቃይ ከተኛሁ በኋላ አንዲት ሴት ጣ
ሳ ባቁላ ሰጥታኝ ኪዳነ ምህረት ሂድ ት
ምርሀለች እዚያው ውጣ አለችኝ። በማ
ግሥቱም እዚሁ ኪዳነ ምህረት መጣሁ
ና ጠበል ተጠምቄ ተመለስሁ።

በዚሁ ጊዜ በትንሣኤ መጽሔት ላይ
አሁን ሥዕሏን እንደምናየው ቅድስት
ድንግል ማርያም በገሀድ እየመጣች አ
ይዞህ ከልጄ አማልድሀለሁ። በሆድህ
ምንም ነገር እንዳያድርብህ አደርጋለሁ
ደዌም አይደርስብህም እያለች ታፅናና
ኝ ነበር። ጠበል መጠመቅ በጀመርሁ
በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ለመዳን
በቃሁ ። ይህም የሆነው በሰኔ ወር 1970
ዓ.ም. ነው።

በፊት ዲያቆን ነበርኩ፡ ጾመኛና ጸሎ
ተኛም ነበርሁ በኋላ ግን ሁሉንም እር
ግፍ አድርጌ ትቼው ነበር። በመጨረሻ
ም ይህ በሽታ ሊደርስብኝ ቻለ ።

አሁን እንደ ቀድሞው በዲቁናም ባ
ይሆን በተቻለኝ ቤተክርስቲያንን እያገ
ለገልሁ ነው ።

### 6 ደምስ ኃይሌ

ትውልዴ በጨቦና ጉራጌ አውራጃ
ነው። ሁለቱም እግሮቼ ሺባ ሆነው ለ
መራመድ አልችልም ነበር። በሰውጉል
በት ታቅፌ ነበር የምንቀሳቀሰው ።

በኋላ እንጦጦ ሐመረ ኖህ ኪዳነ ም
ህረት በሽተኞችን ትፈውሳለች ማለት
ን ሰምቼ እዚሁ ልጠመቅ መጣሁ ።

አስራ አምስት ቀን እንደቆየሁ ሰው
ነቴ ሲድን ከጭኔ በስተቀኝ በኩል ጥቂ
ት አበጠ፣ ከዚያ በኋላ ሐኪም ቤት ሄጄ
ኦፕሬሽን አደረጉኝና ተሻለኝ ።

በዚያው ሺባ የነበረው እግሬ ሊድን
በቃ እኔም ካለኝ ገንዘብ ከሌለኝ በየዓመ
ቱ እየመጣሁ እዚሁ እደርሳለሁ ብዬ
በገባሁት ቃል መሠረት መጥቻለሁ ሺ
ባ የነበርሁት ዛሬ ምንም ሳላነክስ ስራ
መድ ታዩኛላችሁ አሉን።

### 7 አቶ በዛብህ ገብረ ዮሐንስ

በ1952 ዓ.ም ሆዴን ነፍቶኝ ሐኪም
ቤት ብሄድ ጉበትህ ውሃ ስለቋጠረ አንች
ልም ብሎ አሰናበተኝ ።

እኔ ግን ተስፋ ባለመቁረጥ በየሐኪ
ም ቤቱ በመዘዋወር ከዚህም ሌላ አሥ
መራ ሳይቀር ሄጄ ሕክምና ብጠይቅ አን
ችልም ለመዳን ተስፋ ስለሌለህ ፈጽሞ
ለመርዳት አንችልም አሉኝ። ምግብም
ሥጋ እንጀራ፣ አልበላም ፓስታው ተቀ
ቅሎ ውሃውን ብቻ ነበር የምጠጣው ።

ከዚህ ቦኋላ በሐኪም ቤት በኩል ተ
ስፋ ስለቆረጥሁ ወደኪዳነ ምህረት ቤተ
ክርስትያን ለመምጣት አሰብሁ ። ሐሳ
ቤም እድናለሁ ብዬ ሳይሆን ብሞትም
እዚያው እቀበራለሁ ብዬ ስለነበረ ወደ
ኪዳነ ምህረት መጣሁ ።

እዚህ እንደመጣሁ ጠበሉን መጠጣ
ት ስጀምር ሐሞት በብዛት ወጣልኝ።

ከዚያ በኋላ ከያዘኝ በሽታ ድኜ በየዓ
መቱ እዚሁ ኪዳነ ምህረት እየመጣሁ
እንደምታዩኝ በመልካም ጤንነት ላይ
እገኛለሁ ።

በ1952 ዓ . ም ትሞታለህ ተብየ
የነበርሁ እስከአሁን ድረስ በሰላምና በ
ጤንነት እገኛለሁ ሌሎች በሽተኞችን
ሳገኝም በእመቤታችን የተደረገልኝ
ን ፈውስ እየነገርሁ በጠበሉ እንዲፈወ
ሱ እያበረታታሁ እገኛለሁ ሲከፋኝም
ሲያመኝም በጠቅላላው ችግሬን የምነ
ግራት ለእርስዋ ነው።እርስዋም የነገር
ኳትን ሁሉ እስከአሁን ድረስ ትፈጽም
ልኛለች በማለት አቶ በዛብህ ገብረ ዮሐ
ንስ የአስራ ዘጠኝ አመት ትዝታቸውን
ነግረውናል።

### 8. አቶ አሰፋ፣ አማረ

በ1970 ዓ . ም ነሐሴ 1 ቀን በመ
ኪና ፡ መገልበጥ ምክንያት ተለክፌ ታ
ምሜ ነበር። ግማሽ አካላቴ ፈጽሞ በድ
ን ሆነ።

12 ቀን ሆስፒታል ተኛሁ። ምን
ም አልተሻለኝም ። እንዲያውም በዚሁ
ጊዜ ውስጥ ሕይወቴን ፈጽሞ አላውቅ
ም ነበር። ሐኪሙም ባለቤቴን ጠርተው



በኪዳነ ምሕረት ፀበል የዳኑት አቶ አሰፋ አማረ

ሰውየው ምንም ተስፋ የላቸውም ውሰ
ጃቸው ይሞታሉ አላት ባለቤቴም ቢሞ
ትም ቢድንም እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳ
ነ ምህረት ልውሰደው ብላ ይዛኝ ወደዚ
ሁ ጠበል መጣች። አንድ ወር እየተጠ
መቅሁና ጠበል እየጠጣሁ ቆየሁ ከዚ
ያ በኋላ ዳንሁ ብለውናል።

### 9. አቶ ዐቢይ አበራ

በ1951 ዓ . ም አንድ ቀን ሌሊት
ተነስቼ ሽንት ሸንቼ ወደመኝታዬ ተመ
ለስሁ፣ ጥዋት ከአልጋዬ ስነሳ ግማሽ ሰ
ውነቴ ምንም የማይንቀሳቀስ በድን ሆ
ነብኝ። ዓይኔ ፈጠ፣ አፌ ተጣሞ መናገር
ተሳነኝ። ወደአባ ወልደ ትንሣኤ ግዛው
ወሊሶ ሄጄ ጠበል ስጠመቅ ብዙ ጊዜ ቆ
ይቼ ምንም ስለአልተሻለኝ አባ ወልደ
ማርያም ዘንድ ሄጄ ድርሳነ ሚካኤል እ
የደገሙ ሰባት ቀን አጠመቁኝ።

በዚህም ፈጽሞ ልድን አልቻልሁ
ም። ከዚህ በኋላ ደግሞ አባወንድም አ
ገኘሁ ከሚባሉ ባህታዊ ዘንድ ሄጄ ብጠ
ይቃቸው እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ም
ህረት ሄደህ ሰባት ቀን ቆመህ ተጠመቅ
አሉኝ በዚሁ ቦታ መጥቼ ስጠመቅ ተሳ
ስሮ የነበረው ሰውነቴ ባንድ ቀን ተፈታ
በሶስተኛው ቀን ሙሉ ጤንነቴን አግኝ
ቼ ወደቤቴ ተመለስሁ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየበዓሏ ከኪዳ
ነ ምህረት ተለይቼ አላውቅም ሲሉ ታ
ሪካቸውን ዘርዝረው በደስታ ገልጸውል
ናል።

ከአዘጋጁ፣ እርስዎስ ለረዥም ጊ
ዜ የሚያሰቃይ በሽታ ይዞዎታል?

እንግዲያውስ ወደሐመረ ኖህ ኪ
ዳነ ምህረት ብቅ ይበሉና ይሞክሩ፣ አን
ድ ቀን ሊፈወሱ ይችላሉ ሌላም ች
ግር ካለብዎ በእመቤታችን ስም እግ
ዚአብሔርን ቢለምኑ ሊያቃልልዎ ስለ
ሚችል ተስፋ ባለመቁረጥ እምነትዎን
ያጠንክሩ ያን ጊዜ እንደሌሎቹ ዳንኩ
የምሥራች ሊሉ ይችላሉና።

---

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፬ የዞረ

ቀን 1971 ዓ.ም. አንድ አጭር ቄስ መስ
ቀል ሲያሳልሙ ሁለት ሰዎችን ለይተው
ተዋቸው ። ለምን እንዳለፉአቸው ብጠይቅ
ተጣልተው ነው የሚል መልስ አገኘሁ ።
ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የይቅርታ ቤት
ናት እንጂ የቂም በቀል ናትን? ይህ ድርጊት
ቅር የሚያሰኝ ስለሆነ ከዚህ በፊት ለተደረ
ጉት ስህተቶች የደብሩ አስተዳዳሪ ምን ዓይ
ነት ውሳኔና ቁጥጥር እንዳደረጉ እንዲገለጥ
ልን ይህን ደብዳቤ ልከናል ።

ታየ ወርቁ ከፍተኛ 7. ቀ. 27

አቶ ታዬ ወርቁ ርስዎን ያሳዘነ ጉዳይ
እኛንም እጅግ አሳዝኖናል ። በየካቲት 28
ቀን ለተፈጸመው ጥፋት ሌሎች ምእመናን
ጠይቀው ነበር እኛም የደብሩን አስተዳዳሪ
አነጋግረን ጥብቅ ርምጃ የተወሰደ መሆኑን
አስረድተውን በትንሣኤ መጽሔት
ቁ. 22 ላይ አውጥተናል ። እንግዲህ
ከዚያ በኋላ በተደጋጋሚ ለተፈጸሙ አስነ
ዋሪ ተግባሮች የደብሩ አስተዳዳሪ መልስ
እንዲሰጡበት የርስዎን ጥያቄ በዚህ እትም
አውጥተነዋል ። በተጨማሪም ለአቶ ታዬ
የምናሳስበው ካህናትም ሰዎች እንደመሆና
ቸው መጠን ሁሉም ካህናት ከስሕተት ሊ
ነጹ አይችሉምና የአንዳንድ ካህናትን ዝቅ
ተኛ ጠባይ በመመልከት ወደ ቤ. ክርስቲ
ያን ከመሄድ አቋርጣለሁ ማለት ለክርስቲ
ያኖች ተገቢ አለመሆኑን ነው ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በግንቦት ወር 1970 ዓ.ም. የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ





www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን

ከአለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ

## ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ

በአራቱ ጉባኤያት የትምህርት የዕውቀት ችሎታቸውና በዘመኑ በነበረው መንግሥት ባለሙዋልነታቸው በጣም የታወቁት ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ የተወለዱበት ትክክለኛ ዘመን ለጊዜው ተለይቶ ባይታወቅም የትምህርት ይዞታቸውን በይበልጥ ያጠናከሩትና የተጠያቂነትንና የሊቅነት ደረጃ የያዙት ከ1770 (ከአንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ዓመተ ምሕረት) ጀምሮ በመናኔ መንግሥት ተክለ ሃይማኖትና በፈጻሚ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግሥት መሆኑ በታሪክ ተረጋግጧል ።

## የትውልድ አገር

ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ በጎጃም ክ ሀገር የተወለዱ ስመ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ናቸው ።

### ትምህርትና ምርምር

ከአንዱ ወደ ሌላው የትምህርት ጉባኤ በመዘዋወር አራቱን ጉባኤያት ሙሉ በሙሉ አጠናቅቀው የተማሩት ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ በዕውቀታቸውና ከትምህርታቸው ባገኙት ከፍተኛ የአስተዋይነት ችሎታቸው ተመስግነውበታል ፤ ዕውቀታቸውንም በወሬና በዝና ብቻ ሳይሆን በሥራ ገልጸውታል ።

በሐዲስና በብሉይ በመጻሕፍተ ሊቃውንትና በመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ ሊቃውንትን በትምህርት ወልደዋል ።

በዚህ ላይ የቅዱስ ያሬድን ፀዋትወ ዜማና የቁጥር መጽሐፍ አሟልተው የሚያውቁና የሚያስተምሩ ስለነበሩ ሊቅነታቸው ይህ ቀርቶታል ከማይባል ደረጃ የደረሰ መሆኑ ይነገርለታል ።

ዋናዎቹ ወይም መደበኞቹ አስተማሪዎቻቸው ታላቁ ሊቅ መምህር ኤስድሮስ እንዲሁም ከታላላቆቹ ሊቃውንት አንዱ የነበሩት መምህር መልከ ጼዴቅ እንደነበሩ ታውቋል ።

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ሁሉ ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ ጉባኤ ዘርግተው ካስተማርዋቸው ሊቃውንት መካከል ስመ ጥሩ የሆኑት ኢትዮጵያዊ ሊቅ ወልደአብ ወልደ ሚካኤል ይገኙባቸዋል ።

ዓቃቤ ሰዓትን በሰፊው የሚያስመሰግናቸው ሙሉ ትምህርታቸውና ጉባኤ ዘርግተው የተፈለገውን የትምህርት ዓይነት ያለችግር ማስተማራቸው ሳይሆን ከጉባኤ መምህራን ባገኙት ዕውቀት ብቻ አእምሮዋቸውን ሳያፍኑ በግል ስሜትና አቋማቸው ያደርጉት የነበረው የምርምር ሒደትና የአስተያየት ስልት ነበር ።

### በታታሪነታቸው ያስገኙት የዕድገት ደረጃ

ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ በትምህርት በምርምርና በማስተማር በተለይም በተፈጥሮ ባገኙት ብሩህ አእምሮ በሕዝቡም ሆነ በዘመኑ የነበሩት ባለሥልጣኖች ዘንድ ስለታወቁ ዓቃቤ ሰዓት ከሚያሰኝ የመዓርግ ስም ጋር ከፍተኛ የደረጃ ዕድገት ተሰጣቸው ።

ዓቃቤ ሰዓት ለዕድገታቸውና ለመታወቃቸውም ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ዋናው ገና በመማርና አልፎ አልፎም በማስተማር ላይ ሳሉ ጠቢቡ ሰሎሞን በሁለት ሴቶች ላይ እንደ ፈረደው ያለ አስደናቂ ፍርድ መፍረዳቸው መሆኑን የታሪክ ሰዎች ያረጋግጣሉ ።

ይሁን እንጂ የፍርዱን ዓይነት ለጊዜው በሚገባ አድርጎ አጣርቶ የተከታተለው ሰው ባለመገኘቱ ላሁኑ ባይገለጽም ወደፊት ለመግለጽ ተስፋ ይኖረናል ።

በደረጃ ካደጉ በኋላም መሪዎች በሚገኙበት በሚሰጠው ፍርድ ላይ ፍትሐ ነገሥቱን አንቀጽ በአንቀጽ ተከታትለው አንበውና ተርጉመው ይቀጣል ይሞታል ወይም በነፃ ይለቀቃል በማለት በመሪው ስም እየሆኑ ፍርድ የሚሰጡ ባለ ፍትሐ ነገሥት ስለነበሩ ስማቸውም ሆነ የሥራ ድርሻቸው ከፍተኛ ሆኖ ኖሯል ።

## ሥነ ጽሑፋቸው

ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ በትምህርት በምርምርና በማስተማር እንዲሁም በአስተያየትና በፍርድ አሰጣጥ ብቻ ሳይሆን በሥነ ጽሑፋቸው ጥልቀትና ምጥቀት እንዲሁም ጥራት እጅግ የታወቁና የተመሰገኑ ከፍተኛ ሊቅ እንደነበሩ ከታሪካቸውና ከሥራ ውጤታቸው ሊታወቅ ተችሏል ።

ከጻፉዋቸውም መጻሕፍት 1ኛው ሰው በሥነ ፍጥረት አቋሙ እንዴት አድርጎ እንደሚመራና በምርምር ባስገኘውና በየጊዜው በሚያገኘውም ሳይንቲፊካዊ ሒደት ራሱን በራሱ ከጊዜ ወደጊዜ በምን ሁኔታ እንዳሻሻለ ማለት ባለፈው ብቻ ሳይሆን ወደፊትም እንዴት ባለ በረቀቀ ጊዜ የሕይወቱን ተቅዋም ሊያስጌጥና ሊያዳብር እንደሚችል በሰፊው አብራርቶ የሚገልጽ ነው 2ኛው ደግሞ በብሉዓንና ቅዱሳን ሊቃውንት በኒቅያ ጉባኤ የተወሰኑትን የአምስቱን እምነታት ሥርዓታት መሠረት በማድረግ ስለ ዝርዝር ሁኔታው ትንታኔ በመስጠት ያብራሩበት መጽሐፍ ነው ።

ለአምስቱ ሥርዓታተ እምነት መነሻቸውም ሆነ መሠረታቸው ጸሎተ ሃይማኖት መሆኑን ራሱ ጽሑፉ ወይም ኃይለ ቃሉ ሊያረጋግጥ ይችላል ።

## የሃይማኖት አቋማቸው

ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ በትምህርትም ሆነ በተፈጥሮ ስጦታ የተሟላ ችሎታ ቢኖራቸውም በሃይማኖታቸው የሁለት ልደትን ባህል በሚከተሉ ብዙዎች ሊቃውንት ዘንድ መነቀፋቸው ግልጥ ነው ።

ይኸውም የዓቃቤ ሰዓት ከብቴ እምነት የፀጋ ልጅነትን ማለት የሦስት ልደት ባዮችን ባህል የተከተለ በመሆኑ ነው ።

---

ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ሩሲያ ለጉብኝት ሄደው እንደ ነበር ይታወሳል ። የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤ ክርስቲያንም ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ርዳታ እንደምትሰጥ ቃል ገብታ ነበር ። ታዲያ አሁን የተስፋው ቃል ተፈጸመ? ወይስ ከምን ደረሰ ?

ተማሪ አፈወርቅ ምትኬ

ከምስካየ ሕዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የተምሮ ማስተማር የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ፣ አዲስ አበባ

● ተማሪ አፈወርቅ ምትኬ ስለ ቤተ ክርስቲያን ያለህን መልካም ምኞት በደብዳቤህ ላይ በሰፊው ገልጠሃል ። ስለዚህም እናመሰግንሃለን ። ቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ ሩሲያ በሄዱ ጊዜ የተሰጣቸው ተስፋ በተግባር ይገለጥ ዘንድ ፕሮጀክት ተዘጋጅቶ ወደ ሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ተልኮአል መልሱ በመጣ ጊዜ የተስፋው ቃል በተግባር ይገለጣል ይህም ሩቅ አይሆንም ።



# ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች

ካሁን ቀደም በተላለፈው ጽሑፍ መጥምቁ ዮሐንስ የተረሱ ሕዝቦችን እያስተማረ ከገጠር ወደ ከተማ መግባቱንና ፣ በከተማም ውስጥ በሚገኙት የተረሱ ሕዝቦች ላይ የሚፈጸመውን ግፍና በዚያን ዘመን የነበረውን ቅጥ ያጣ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንዳጋለጠ መጻፋችን አይዘነጋም ።

በዚህ ጽሑፍ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ተረሱ ሕዝቦች ሐዋርያትን ልካለችን? የተላኩትስ ሐዋርያት ተልእኮአቸውን ፈጽመዋልን ? ለሚለው ጥያቄ ቀደም ያለውን ታሪክ በመመርኮዝ እናቀርባለን ።

አለቃ ታዬ የጻፉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ እንደሚለው "ብዙ ነገዶች ፣ ልዩ ልዩ እምነታቸውን ፣ ባህላቸውንና ስነሥርዓታቸውን እየያዙ በየዘመኑ ከአገራቸው እየፈለሱ ወደኢትዮጵያ ምድር ገብተዋል። ከነዚህም መካከል ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺህ ዓመተ ዓለም ግድም የሥጋዊ ጥበብና የመንፈሳዊ ዕውቀት ጠለቅ ብሎ የገባቸው የእሥራኤል ካህናት ታቦተ ጽዮንን ተከትለው ሲመጡ የኦሪትን እምነት ፣ ባህልንና ሥነ ሥርዓትን ፣ ይዘው በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ሰሜን ዳርቻ ለመጀመሪያ ጊዜ ገብተዋል ።

ይኸውም በገጠሩ ሳይሆን መናኸሪያቸውን በየከተማው እንዳደረጉ ይኸው ታሪክ ያብራራል በዚያን ዘመን የጥበብና የዕውቀት መፍለቂያ ወደነበረችውና የመንግሥት መቀመጫ ወደነበረችው ወደ አክሱም ከተማ መግባታቸውንም ታሪኩ ይናገራል። በዚህ አኳኋን የመጡት የእሥራኤል ካህናት የኦሪትን እምነት ፣ ባህሉንም ሆነ ሥርዓቱን ያስተማሩትና የሰበኩት በዘመኑ ለሚገኙት ነገሥታትና ግብረ አበሮቻቸው ፣ በከተማ ለሚኖሩ ታላላቅ ሰዎች እንጂ በየገጠሩ ለሚገኙት ፣ በየጠረፉና በቀይ ባሕር አካባቢ ለሚኖሩ ለተረሱ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን አምላክነት ፣ የሃገርን አንድነት አላስተማሩም ።

መሪዎችም ቢሆኑ የኦሪትን እምነት ፣ ሥነሥርዓቱንም ሆነ ባህሉን በቤተ መንግሥታቸው አፍነው ላስተዳደራቸው መጠቀሚያ ከሚያደርጋቸውም ሌላ ካህናቱ ወደ ተረሱ ሕዝቦች ዘንድ ሄደው እንዳያስተምሩ በሹመትና በልዩ ልዩ ስጦታ ስለሚደልሏቸው በገጠር አላስተማሩም ።

የክርስትና እምነት በጃንደረባው አማካይነት ወደኢትዮጵያ መጥቶ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ተሸፍኖ አቡነ ሰላማ እስከተነሳበት እስከ 330 ዓ.ም. ድረስ ሕዝብ ሳያውቀው ኖረ በአቡነ ሰላማም ጊዜ ቢሆን የክርስትና እምነት በነገሥታቱ ሥር ሁኖ ያስተዳደራቸው መጠቀሚያ ከመሆን በቀር ለብዙኃን ሕዝብ አልተዳረሰም ነበር ።

ይህም ዘመን ሰዎች የተዋረዱበት ፣ የተረሡ ሕዝቦች የተናቁበት ፣ የክርስትና እምነት ያልተዳረሰበት ፣ ዕውቀት ያልተስፋፋበት በጠቅላላው ፡ የተጕሳቆለ ኑሮ የሚኖርበት ዘመን ነበር ለማለት ይቻላል ። በአንፃሩ ደግሞ ጥቂት የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ፤ የአድባራትና የገዳማት አስተዳዳሪዎች ወደ ተረሱት ሕዝቦች ሄደው ትምህርት ሳያዳርሱ ለቤተ መንግሥቱና ለግብረ አበሮቻቸው በከተማ ተቀምጠው የክርስትናን እምነት የሚያንበባርቁበት ዘመን እንደነበር ይነገራል ።

ለምሳሌ የደብረ ቢዘን ገዳም ከተመሠረተ አያሌ ዘመን አልፈዋል በገዳሙም ብዙ መነኮሳት ይገኛሉ የገዳሙም አስተዳደር በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት የመሠረቱትን ሥነ ሥርዓት ተከትሎ በውስጡ የሚገኙ መነኮሳት እኩል ሠርተው እኩል እንዲበሉ በማድረጉ የሚመሰገን ነው ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ ዘመናት ሲያሳልፍ መነኮሳቱን በወንጌል ትምህርትና በስብከት ዘዴ እያሰለጠነ ፤ ኮርስ እየሰጠ ፤ በአካባቢው ወደሚገኙ ወደተረሱ ሕዝቦች ዘንድ በመላክ እሱም ሆነ ሌሎቹ ገዳማት ቢያስተምሩ ኖሮ በቀይ ባህር አካባቢና በየገጠሩ የሚኖሩት የተረሱና የተለያዩ ነገዶች ወዳጅና ጠላታቸውን ለይተው ስለሚያውቁ በሃይማኖት እያሳበቡ በቀይ ባህር በኩል ተሹለክልከው ገብተው ሕዝቡን በጐሳና በሃይማኖት የሚከፋፈሉበትን መንገድ አያገኙም ነበር ።

ታሪክ እንደሚነግረን በየዘመናቱ በቀይ ባሕር በኩል ጠላቶች እየተፈራረቁ እምነትን ምክንያት በማድረግ ሕዝቡን እየከፋፈሉ ሀገሪትዋን ሲያጠቁ ኑረዋል ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ ወደ ታሪክ መለስ ብሎ ማተኮር ያስፈልጋል ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ያሉት እውነተኛ የታሪክ ጸሐፊዎችና የታሪክ አዋቂዎችም የሚሉትን ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን ፦

ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ ሆነ ከዚያ ቀጥሎ ባለው ዘመን ጀምሮ በመጀመሪያም የኦሪትን እምነት ቀጥሎም የክርስትና እምነትን ተቀብሎ በኢትዮጵያ ሰሜን ያለው ሕዝብ ይኖር እንደነበር ግልጽ ነው ምንም እንኳን እምነቱና ሥልጣኔው ለተረሱ ሕዝቦች ባይዳረስም ይህ አካባቢ የኢትዮጵያ የሥልጣኔና የባህል ምንጭ መሠረት ሆኖ እንደቆየ ታሪክ ይመሠክራል ይኸውም በ16ተኛውና በ17ኛው ምዕተ ዓመት አቶማን ቱርኮች በሃይማኖት አማካይነት በዚሁ አካባቢ ጦርነት አካሂደዋል አሸንፈውም የዳህላክ ደሴቶችንና ምጽዋን ለመያዝ ችለዋል የአቶማን ቱርክ ኃይል በተዳከመበት ጊዜ በቦታው ግብጽ ተተካች ግብጽም እንደጐርጐርዮሳውያን አቆጣጠር በ1868 ዓ.ም. የምፅዋን ወደብ በመያዝ ወደ መሃል አገር ለመስፋፋት ሞክራ ነበር ይሁን እንጂ ነፃነት አፍቃሪ የሆኑት ኢትዮጵያውያን ሁሉንም ድል አድርገው ወደመጡበት እንደመለስዋቸው የኢትዮጵያ ታሪክ ይናገራል ።

አሁን የተነሳነው በየጊዜው የተደረጉትን ጦርነቶች ለመናገር አይደለም እነዚህ ሁሉ ጦርነቶች በአገሪትዋ ላይ ሊፈጸሙ የቻሉት ቤተ ክርስቲያን በየገጠሩና በየጠረፉ በባሕሩ ወደብ ወደሚገኙት ወደተረሡ ሕዝቦች ሐዋርያትን እየላከች እንዲያስተምሩ ባለማድረግዋ ነው እነዚህ ሕዝቦች በየጊዜው አስተማሪ እየተላከላቸው የህሊና ንቃት አግኝተው የአገራቸውን አንድነት አውቀው ቢነቁና ቢደራጁ ኑሮ ወዳጅና ጠላታቸውን ለይተው ስለሚያውቁ በሃይማኖት ሰበብ በምጽዋ በኩል ተሹለክልከው የሚገቡትን ጠላቶች መግቢያ ቀዳዳ ያሳጥዋቸው ነበር ።

ነገር ግን ባለመንቃታቸውና ባለመደራጀታቸው በዚያን ዘመን የነበረውም አስተዳደር ለረሃብ ፣ ለችግር ፣ ለበሽታ ፣ ለመሃይምነት አጋልጦ ስለሰጣቸው አንዳንዶቹ ተሹለክልከው ከሚገቡ ጠላቶቻችን ጋር እየተባበሩና መንገድም እየመሩ በማሳየት በአገሪትዋ ላይ በየጊዜው ለሚፈጸሙት ጦርነቶች ዋና ምክንያት ሁነዋል ።

ባለፉት ዘመናት የነበሩ መንፈሳውያን መሪዎች እራሳቸውን ወዳዶች ስለነበሩ ቤተ ክርስቲያን ትሰጥ የነበረው ትምህርት በከ

ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የነበረው እንዳልነበረ እንዳይሆን

የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችዋ ለራስዋ ጥቅም ይዋሉ፣ በሚል ርእስ ከራደ አስረስ
በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 22 ፡ 1971 ዓ.ም የታተመውን አስተያየትና ጥቆማ አንድ ባንድ ተመልክቼዋለሁ።—

ባቀረቡት አስተያየትም ከመጀመሪያው ተራ ቁጥር በስተቀር በጠቅላላው በበኩሌ የሚደገፍና ጊዜ ሳይሰጠውም የሚመለከተው ክፍል ሊያስብበ የሚገባ ነው እላለሁ።

ራደ አስረስ ያቀረቡትን አስተያየት ምናልባትም ያልተመለከተ አንባቢ ይኖራል በማለት አንደኛው ቁጥር በጠቅላላ በድጋሚ ያቀረብኩት ሲሆን ቃሉም የሚለው እንዲህ ነው።

«በየክፍላተ ሀገሩ የሊቀ ጳጳሱ መንበር በሆነው ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ከዕሳት ከሌባና ከመሳሰሉት አደጋዎች መካላከል የሚችል ሰፊ ቤት ማሠራት የየገዳማቱን የየአድባራቱንና የየአብያተ ክርስቲያኑን መጽሐፍት ሥዕላትና ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ በሦስት ኰፒ መመዝገብ ከተመዘገቡ በኋላ በጥንታዊነታቸውና በጥራታቸው ጐብኝዎችን ያስደስታሉ ቱሪስቶችን ይስባሉ ተብለው የሚታመንባቸውን መጻሕፍትና ንዋያተ ቅድሳት በመንበረ ሊቀ ጳጳሱ ቅጥር ጊቢ ወደ ተዘጋጀው የቅርሳ ቅርስና ንዋየ ቅድሳት ማደራጃ ክፍል ወስዶ በተዘጋጀላቸው ልዩ ክፍል ማስቀመጥ ሲቀመጡም የእንዱን ገዳም ዕቃ ከሌላ ገዳም ዕቃ ጋር እንዳይዘበራረቅና ሁኔታው መልክ እንዳያጣ ለእያንዳንዱ ገዳም ዕቃ የተለየ ክፍል መስጠት ለጐብኝዎችና ለአጥኚዎችም አመች ይሆን ዘንድ ቅርሶች የማነኛው ገዳም እንደሆኑ ታሪካቸውንና ጥንታዊነታቸውን በአጭሩ የሚገልጥ የሰሌዳ ጽሑፍ ከጐናቸው ማስቀመጥ ያስፈልጋል፤ ከዚህም ሌላ ዕቃዎቹ የተመዘገቡበት ሦስት ኮፒ አንደኛው ዕቃዎች ከተነሱበት ቦታ ሲቀመጥ 2ኛው ከዕቃዎቹ ጋር 3ኛው በጠቅላይ ቤተ ክህነት መዝገብ ቤት መቀመጥ ይኖርበታል፤ ይህም ዕቃዎቹን በሚገባ ለማስጠበቅና ለመቆጣጠር አመች ይሆናል ፣ይህንንም ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል፤ ምንአልባትም ቅርሶቹ ከአድባራቱና ከየገዳማቱ ተለቅመው ይወሰዱና በሚገባ ተጠብቀው ለቤተክርስቲያንዋ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ወደ ተዘጋጀላቸው አስተማማኝ ስፍራ ይወሰዱ ሲባል የገዳማቱና የአድባራቱ ኃላፊዎች ካህናትና ምእመናን ፈቃደኞች ላይሆኑ ይችላሉ፤ ለዚህም መጻሕፍቱ ከዕሳትና ከሌላ አደጋ በማያስተማምን ዕቃ ቤት ተጥለው ከዚህም የባሰ ከአንዱ ገበዝ ቤት ወደ ሌላ ገበዝ ቤት በመንከራተት ጢስ ጠጥተው በአይጥና በሌሊት ወፍ ተቀኍጸጽለው ከሚጠፉ ሌሎችም እንደስዕል፣ መስቀልና ቅርጻ ቅርጽ ያሉት በዝናምና ፍሳሽ ርሰው በአፈር ተበልተውና ዝገው ከሚበላሹ ይልቅ በአንድ ስፍራ ተደራጅተውና በሚገባ ተጠብቀው ለትውልድ ቢተላለፉና ለቤተ ክርስቲያንም የገቢ ምንጭ ቢሆኑ የተሻለ መሆኑን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስረዳትና ማሳመን የመጀመሪያው ርምጃ መሆን ይኖርበታል» ሲሉ አትተዋል።—

ባሁኑ ከሥራ መፈክሮቻችን አንዱ ልማት ከገጠር ወደ ከተማ እንጂ ከከተማ ወደ ገጠር መሆን የለበትም ብለን የምናምን ከሆነና መፈክሩም በሥራ ይተርጐም ከተባለ ይህ ከላይ ሀሳብ ሰጪው፣ ያቀረቡት አስተያየት ቦታ ያለው አይመስለኝም እሳቸው አተኩረው የተመለከቱት ተፈላጊ ነገሮች ከቆላም ሆነ ከደጋ በዚያው በአዲስ አበባ ተማልቶ እንዲቀርብላቸው ፈላጊ ይመስላሉ ፣ በዚህ ጽሑፋቸው የገዳማቱ ንዋየ ቅድሳት በአንድ ቦታ ማከማቸት ለቱሪስት ያመቻል የገቢ ምንጭም ለቤተ ክርስትያኑ ይፈጥራል ብለዋል ፣ ነገር ግን ይህ አባባል ከዕውነት የራቀ ነው። ምክንያቱም አንድ ቱሪስት በከፍተኛ ወጭ የታሪክ ቦታዎችን በየቦታቸው ከሀገሩ የተፈጥሮ አቀማመጥና ውበት ጋር ለመጐብኘት በፕሮግራም ከሀገሩ ሲወጣ እነዚያ የሚፈልጋቸው ቅርሶች በአዲስ አበባ ተከማችተው ካገኛቸውና በአስጐብኚው አመካይነትም ጐብኝቶ ወደ ሀገሩ ከሚመለስ በስተቀር ምን በወጣው ለአውቶቡስና ለአይሮፕላን ወጭ በማውጣት ላሊበላን፣ አክሱምንና ሌሎችም የታሪክ ቦታዎች ሊጐበኝ ይችላል? መልሱ አይችልም ነው፤ ይህ ሲሆን እንግዲህ የሚቀረውን የውጭ ምንዛሪ ያስቡት፤ በዚህ ምክንያትም ቱሪስት ተቀባይ የሆኑ ሆቴል ቤቶች የሚደርስባቸውን ኪሳራ ያስቡት፤ የመጣንበትን ታሪክ መለስ ብለን የተመለከትን እንደሆንም ሌላ ከባድ ነገር ትውስ ሊለን ይገባል ይኸውም ግራኝና ጉዲት ቤተክርስቲያንን ጠራርገው ለማጥፋት በተነሱ ጊዜ ያወደሙዋቸውን የታሪክ ቅርሶቻችንን እናስታውሳቸው፤ ላሁን ትውልድ ጭላንጭል ሊገኝ የተቻለው በተለያዩ ገዳማትና አድባራት በመገኘታቸው ሲሆን እንደ ጸሐፊው አስተሳሰብ ባንድ ቦታ ተከማችተው ቢሆን ኖሮ ግን እነዚያ ጠላቶቻችን እንደጀመሩት ቢያወድሟቸው የአሁኑ ትውልድ ምን ይውጠው ነበር ታሪክ አልባ ሆኖ መቅረትና እንዲህ ነበር ማለት ብቻ ነው።

ይህን ብቻ አይደለም ሌላ ጠለቅ ብለው ያላስታወሱት አለ ለአደጋ ቀጠሮ ስለሌለው ቅርሶቻችን ባንድነት በተከማቹበት ቦታ እንደዓይን ብሌን በምንጠብቃቸው ቅርሶቻችን አደጋ ቢደርስ መጭው ትውልድ ከማን ይካሳል።?

ራደ አስረስ ቅርሶቻችን ካንዱ ቢጠፋ ባንዱ እንዲገኙ በ 3 ኮፒ የተባዛ ስለሆነ አያስጋም ሊሉ ነው ፣ ነገር ግን ማን እንደጥንቱ ቅርስ? የጥንቱ ቅርስ እኰ ላሁን ትውልድ ከሚያስደንቀው አንዱ አባቶቻችን ለባሕላቸው አጠባበቅ ምን ያህል ጥበባዊ ይዞታና ቅናት እንደነበራቸው መረዳቱ ነው።

ይህንን ብቻ አይደለም ከወርቅና ከብር እንደዚሁም ከዕንጨት የተሰሩ ቅርሳ-ቅርሶችስ በምን አይነት ይጠበቁ ነው የሚሉት? በአጠቃላይ አነጋገር ይህ ዓይነት ጥቆማና አስተያየት ተቀባይ የለውም ከማለት በስተቀር በይበልጥ ለማስረዳት የአንባቢዎችን ዓምድ ማጣበብ ስለ.ማሆን ሀሳቤን ለመግታት ያህል ስለቅርሶቻችን አጠባበቅ ያለኝ አስተያየት ቀጥሎ ያለው ነው።

1ኛ፡- ከልዩ-ልዩ ዓይነት የተሠሩ ቅርሳ-ቅርሶቻችንና ጽሁፎችን የታሪክ ቦታቸውን ይዘው ባሉበት መጠበቅ አለባቸው።

2ኛ፡-የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ ቤት እንደአለፈው አስተዳደር ተመልካችና አዳማጭ ሳይሆን፣ ለክፍሉ የታሪክ ቅርስ ተጠያቂ ስለሆነ ፡ እጅጌውን ሰብስቦ አድርጐ በስራው ውስጥ በመግባት ተዘዋዋሪ የቅርሳ ቅርስ ጥበቃ ቡድን አቋቁሞ በየታሪክ ቦታዎች በመዘዋወር የታሪክ ዕቃዎችን ሕልውና መቆጣጠር እንዲመዘገቡም ማድረግ

3ኛ-በየገዳማቱና አድባራቱ የሚገኙ የሰበካ ጉባኤ አባላት ለቅርሳ-ቅርሶቹ ጥበቃ እንዲያስቡበት የተለየ ቤትም እንዲሠራላቸው መገፋፋትና ማበረታታት፣ ምዕመናኑንም አስተባብሮ ጥቅሙን ማስረዳት ።

4ኛ፡—ተዘዋዋሪ የቅርሳ-ቅርስ ጥበቃ ቡድንም በየታሪክ ቦታዎቹ ያገኛቸውን የታሪክ ቅርሶች ከነመረጃቸው በፎቶግራፍ በትንሣኤ መጽሔት ለአንባብያን ማቅረብ።

5ኛ፡—የቱሪስት መሥሪያ ቤት ለጐብኝዎች እንደሚያዘጋጀው ያለ ካርድ ያንዳንድ የታሪክ ቦታዎችን በካርድ በማውጣት የገቢ ምንጭ መፍጠር።

በበኩሌ ያለኝ አስተያየት ይህ ሲሆን፣ ጥፋትም ሆነ ልማት የጋራ ስለሆነ ራደ አስረስ ባቀረብኩት አስተያየት ቅር እንደማይሰኙ በማመን ነው ።

ከሙሉጌታ ኃይለሥላሴ
በሲዳሞ ክፍለሀገር አዋሳ።



# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

## ስለ ምሥጢረ ሥላሴ

ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስትነታቸው በስም ፣ በግብር ፣ በአካል ነው ። እነዚህንም እንደሚከተለው በቅደም ተከተል እናቀርባለን ፡-

### ሀ/ የስም ሦስትነት

የሥላሴ የስም ሦስትነት አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ በመባል ነው ። ይህ ስለተባለ ግን አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አንልም ። ይህም ስም መለዋወጥና መፋለስ ሳይኖርበት ማለትም አብ በመሠረቱ አብ ይባላል እንጂ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም ፡ ወልድም እንዲሁ ወልድ ቢባል እንጂ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም ፡ መንፈስ ቅዱስም ወልድ ወይም አብ ተብሎ የመጠራትን ስም አይወስድም'' ሲል አግናጢዎስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ አስረድቶአል ። (አግናጢዎስ ክፍል 1)

ሥላሴ በስም ሦስት ናቸው ፣ በአምላክነት ግን አንድ ነው ። ይህንም አባባል በማዕናት ረገድ ቄርሎስ የተባለው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሠለስቱ (ሦስት) ስም አሐዱ (አንድ) እግዚአብሔር ሲል አስረድቷል ።

### ለ/ የግብር ሦስትነት

የሥላሴ የግብር ሦስትነት አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ በመሆን ነው ። ይኸውም የአብ ግብሩ መውለድና ማስረፅ ስለሆነ አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርፅ እንጂ እንደወልድ አይወለድም እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም ፣ ወልድም ቢወለድ እንጂ እንደአብ አይወልድም ፣ አያሠርፅም ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም ፣ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ቢሠርፅ እንጂ እንደ አብ አይወልድም ፣ አያሠርፅም ወይም እንደወልድ አይወለድም ፣ ሲል የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አትናቴዎስ ጽፎአል ።

### ሐ/ የአካል ሦስትነት

የሥላሴ የአካል ሦስትነት አብ በወላዲነቱ ፣ ፍጹም ገጽ ፣ ፍጹም መልክ ፣ ፍጹም አካል አለው ። ወልድም በተለየ አካሉ በተወላዲነቱ ፍጹም ገጽ ፣ ፍጹም መልክ ፣ ፍጹም አካል ያለው ሲሆን መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ በሠራፂነቱ ፍጹም ገጽ ፣ ፍጹም መልክ ፣ ፍጹም አካል አለው ። (አትናቴዎስ ክፍል 5)

ሥላሴ እንዲህ ባለ ስም ፣ እንዲህ ባለ ግብር ፣ እንዲህም ባለ አካል ሳይቀዳደሙ ቃልና እስትንፋስ ከልብ እንደሚገኙ ስማቸው ከአካላቸው አካላቸውም ከስማቸው ሳይቀድም በሰማይም በምድርም በአፍአ ፣ በውስጥ ምሉዓን ሆነው የነበሩ ፣ ያሉና ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው ። (ጎርጎሬዎስ ገባሬ ምንክራት ክፍል 1)

2ኛ አንድነት በሦስትነት .

የሥላሴ አንድነታቸው በባሕርይ ፣ በመለኮት ፣ በመንግሥት ፣ በእግዚአብሔርነት፣ ወይም በአምላክነት ነው ። ሥላሴ በመንግሥት በባሕርይ ፣ በመለኮት አንድ ናቸው ። እንግዲህ ሦስት የሚያደርጋቸው አካል ሲሆን አንድ የሚያደርጋቸው ባሕርይ ፈቃድ ነው ።

ይኸውም አካል በአካል ህልው ሆኖ በአንድ ልቡናነት በአንድ ቃልነት በአንድ እስትንፋስነት ስለሚኖር ነው ማለትም አብ በፍጹም ገጹ በፍጹም አካሉ ልብ ነው ፡ ሌላ ልብ የለውም ወልድም በፍጹም ገጹ በፍጹም አካሉ ቃል ነው ሌላ ቃል የለውም መንፈስ ቅዱስም በፍጹም ገጹ በፍጹም አካሉ እስትንፋስ ነው ፡ ሌላ እስትንፋስ የለውም ሲሉ ቴዎዶጦስ ፣ ጎርጎሬዎስና ድዮናስዮስ ተናግረዋል ።

ስለዚህም ''አብ በልብነቱ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው ፡ ወልድም በቃልነቱ በአብና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው መንፈስ ቅዱስም በእስትንፋስነቱ በአብና በወልድ ህልው ነው'' ሲል ፊላታዎስ ዘእስክንድርያ ተናግሮአል ። በግልጽ አነጋገር አብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡናቸው ነው ፣ ወልድም ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው ማለትም በአብ ልቡናነት ሦስቱም ያስባሉ በወልድ ቃልነት ሦስቱም ይናገራሉ በመንፈስ ቅዱስም እስትንፋስነት ሦስቱም ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ ። በጠቅላላው ይገነዛዘባሉ ብለን እናምናለን በማለት አቡሊዲስ ዘሮሚ አስረድቷል ።

ቄስ መክብብ አጥናው

ይቀጥላል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

## 300 ካህናት ሠለጠኑ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን በ1971 ዓ.ም. እቅዱ መሠረት ከሐምሌ ወር ጀምሮ በትግራይ ፣ በወሎ ፣ በጐንደር ፣ በጐጃምና በሸዋ ሀገረ ስብከት ለ300 ካህናት የ3 ወር ትምህርት ሰጥቷል ።

ለካህናቱ የጤና አጠባበቅ ዘዴ ፣ የርሻና የጓሮ አትክልት አጠቃቀም ፣ የስብከት ፣ ዘዴ ፣ ትምህርተ አበ ነፍስና ሕዝበ ክርስቲያኑን በሰበካ ጉባኤ አባላት እንዲሆኑ የማስተባበር ትምህርት ተሰጥቶአቸዋል ።

እነዚህ ካህናት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በየሀገረ ስብከቱ የሰበካ ጉባኤ አመሠራረትና አሠራርን ለማጠናከር አላፊነት እንደሚኖርባቸው ተረጋግጧል ።

ለወደፊቱ ኮሚሽኑ በ14ቱ አህጉረ ስብከት ተመሳሳይ ኮርስ ለካህናቱ የሚሰጥ መሆኑን ኮሚሽኑ ገልጧል ።

## የክርስቲያን በጎ አድራጎት የልማት ድርጅት ለመሠረተ ትምህርት ርዳታ ሰጠ

መሐይምነትን ከአብዮታዊት ኢትዮጵያ ለማጥፋት ለተጀመረው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ማስፈጸሚያ የሚውል የክርስቲያን በጎ አድራጎት የልማት ድርጅት አሥር ሺህ ብር ርዳታ ሰጠ የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶክተር ኀይቶም ጴጥሮስ የአሥር ሺህ ብር ቼክ ካስረከቡ በኋላ ባደረጉት ንግግር፡- የክርስቲያኖች በጎ አድራጎት የልማት ድርጅት እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በደረሱት በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች መርጃ ከአንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር በላይና ተመሳሳይ ግምት ያለው የምግብና የቁሳቁስ ርዳታ ማድረጉን ገልጠው አሁንም ለመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ያደረጉት አስተዋጽኦ የመጨረሻ አለመሆኑን አስረድተዋል ።

አዲስ ዘመን ቁ. 290 ነሐሴ 19 ቀን 1971 ዓ.ም.

## ክርስቲያኖች ገለልተኞች መሆን አይችሉም

ወልፍስ በርግ ጀርመን፡- ክርስቲያኖች በጭቁኖች ጎን መቆም አለባቸው እንጂ ገለልተኛ ሊሆኑ አይችሉም ሲሉ የቀድሞው የችሊ ሉተራዊ ጳጳስ ሄልሙት ፍሬንዚ በቅርቡ በወልፍስበርግ በተደረገው ሐዋርያዊ በዓል ላይ ባሰሙት ንግግር ገለጡ ፣ ሰብአዊ መብትና ክብርን ለማስጠበቅ የሚታቀደው ተግባር ሁሉ ነገረ መለኮታዊ መሠረት እንደሚያስፈልገው ጳጳስ ፍሬንዝ ያምናሉ ።

ስለ ሰብአዊ መብት መሥራት የሚጀምር ማንኛውንም ሰው ተቃውሞ እንደሚገጥመው ማወቅ አለበት አብያተ ክርስቲያናት ሁልጊዜ ከተቃውሞ ራሳቸውን ለማገለል በሚያደርጉት ጥረት ልክ አይደሉም ። ይህ ሳይሆን ለሰላምና ለፍትሕ መሥራት ይኖርባቸዋል ፣ ሰላምና ፍትሕ በየትም ቦታ ተረስተዋልና በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ ስለ ሰላምና ፍትሕ መናገር የአብያተ ክርስቲያናት ሥራ ነው ።

የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን የዜና አገልግሎት ቁ. 22 79
ነሐሴ 7 ቀን 1979 (እ.ኤ.አ.)

## የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በአውስትራልያ

ሜርበልን፡- የኦርቶዶክስ አ ክርስቲያናት በአውስትራልያ ውስጥ ከፍተኛ ዕድገትን በማሳየት ላይ እንደሚገኙ ተገለጠ። ለምሳሌ በ1947 ዓ . ም 20.000 አባላት ሲጨመሩ በ1976 ዓ.ም. 700. 000 አባላት ተጨምረዋል፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል የተፋጠነ ዕድገት ከታየ አውስትራልያ ወደፊት ኦርቶዶክሳዊት ሀገር እንደምትሆን ይገመታል ። በአውስትራልያ የሚገኙ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የግሪክና የግብጽ ናቸው ። ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ማንኛውም አገልግሎታቸውንና ትምህርታቸውን በግሪክና በዐረብኛ ይፈጽማሉ። ከዚህም የተነሳ ሜርበልን በዓለም ውስጥ ሦስተኛ የግሪክ ተናጋሪ ከተማ ሆናለች ሲል ኢንተርናሽናል ሪቪው ኦፍ ሚሲዮን ቁ . 269 ቅጽ 48 ገለጠ

ተሞችና ለም በሆኑ መንደሮች ብቻ በመወሰኑ የሚገባትን አገልግሎት ለሕዝብ እንዳላበረከተች ይታወቃል ።

ክርስቶስ ሲያስተምር ''እናንት የዓለም ብርሃን ናችሁ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ሂዱና አስተምሩ መብራት እንዲያበራ ከተፈለገ ከእንቅብ በታች አያስቀምጡትም ከእንቅብ በታች ከተቀመጠ ግን በጨለማ ላሉት አያበራም በመቅረዙ ላይ ካኖሩት ግን በቤት ላሉት ሁሉ ያበራል'' ሲል አስተምሯል ክርስቶስ ይህን ትምህርት ለሐዋርያት ያስተማረው ብርሃን ባለበት ሥፍራ እየሄዱ ሌላ ብርሃን እንዲጨምሩ አይደለም ።

የዕውቀት ብርሃን አጥተው ፣ በመሃይምነት ጨለማ ውስጥ ተውጠው ፣ ለሚማቅቁና የኑሮ ቀንበር ከብዶአቸው ወደሚጨነቁ ወደተረሱ ሕዝቦች ሄደው የዕውቀት ብርሃን እንዲያሳዩዋቸው ነበር ሠርተውም ኑሮአቸውን የሚመሩበትን መንገድ እንዲቀይሱላቸው ነበር ። ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስን ቃል በመከተል ሐዋርያትን ወደተረሱ ሕዝቦች ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ መላክና ትምህርት ማዳረስ ይገባታል ዓላማዋ ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# ቤተክርስቲያንና ቅርሶችዋ

የደብረ ሊባኖስ ገዳም በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተመሠረተ ለመሆኑ በታሪክ ጸሐፊዎች ተረጋግጦአል ። ይሁን እንጂ ገዳሙ በዚህ መቶ ክፍለ ዘመን የተመሠረተ ለመሆኑ ተጨባጭ የሆኑ የታሪክ ቅርሶች ቡን ኢየሱስ ሞአ ገዳም ያሉ ቦታዎቹ ለጠላት በጣም አመች ባለመሆናቸው እስከ አሁን ድረስ እጅግ አስደናቂ የሆኑ የታሪክ ቅርሶች በውስጣቸው ተከማችተው ይገኛሉ ።



በደብረ ሊባኖስ የሚገኝ ጥንታዊ መስቀል

በጣም ጥቂቶች ናቸው ።

ይህም የታሪክ ቅርስ ሊገኝ ያልተቻለበት ምክንያት ብዙ ነው ። ከግራኝ መሀመድ ወረራ በፊት የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ጥፋትና ድምሳሴ ደርሶባቸዋል ። የመቃጠልና የመደምሰስ አደጋ ከደረሰባቸው ታላላቅ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ነው ።

ከዚህ ገዳም ጋራ በተመሳሳይ ጊዜያት የተመሠረቱ እንደ ሐይቅ እስጢፋኖስ የአ

የደብረ ሊባኖስ ገዳም ግን እንደ ጥንታዊነቱ መጠን በጣም ጥንታዊ የሆኑ የታሪክ ቅርሶች በውስጡ አይገኙም ነገር ግን ለምልክት ያህል ከመጻሕፍትም ሆነ ከመስቀሎች ለምሳሌ ያህል ይገኛሉ ።

በ1970 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሄድ በዋናው ቤተ ክርስቲያን ምድር ቤት በሚገኘው እቃቤት ውስጥ የተቀመጡትን መጻሕፍት ካታሎግ ሳደርግ ሰንብቼ ነበር ። ይህንን ሥራ እየሠራሁ ለአንድ ሳምንት በተቀመጥኩበት ወቅት በዕድሜ በጣም ጥንታዊነት የሌላቸው ከወርቅ ፣ ከብር ፣ ከነሐስ ፣ ከመዳብ ፣ ከብረታ ብረት የተሠሩ ዋጋቸው እጅግ ውድ የሆኑ የታሪክ ቅርሶች በብዛት ለማየትና ለማጥናት ችየአለሁ ።

የተመለከትኋቸው የታሪክ ቅርሶች ከሞላ ጐደል ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ይሆናል ።

| | |
|---|---|
| ሥዕለ አድህኖዎች | ጽንሐዎች |
| ጽዋዎች | መስቀሎች |
| ዓህሎች | ኩስኩስቶች |
| መሶሪያዎች | ገምጃዎች |
| ከበሮዎች | መጐናፀፊያዎች |
| መቋሞያዎች | ጭራዎች |
| ጻናጽሎች | |
| አልባሳት | አክሊሎች |
| ጥላዎች | መስበ ወርቆች |
| ድባቦች | ምንጣፎች |
| መቅረዞች | መናብርቶች |
| | ማህፈዶች |
| | ማህተሞች |

ከላይ ከጠቀስኳቸው የታሪክ ቅርሶች መካከል በጣም ጥንታዊነት ያላቸው ሁለት መስቀሎች ብቻ ናቸው 1ኛ ከብረት የተሠራ በሁለት ገጽ ልዩ ልዩ ሥዕሎች ያሉት አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሕይወት ሳሉ የእጃቸው መስቀል ነበር የሚባልና በአሁኑ ጊዜ ገድል አንባቢው መነኩሴ በሽተኞችን እያጠመቁ በሽተኞችን የሚፈውሱበት የብረት መስቀል ነው ።

2ኛ በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ለደብረ ሊባኖስ የተሰጠነው እየተባለ የሚነገርለት ከመዳብና ከነሐስ የተሠራ ክብደት ያለው ጥንታዊ መስቀል ነው ይህ መስቀል አቀራረፁ ሳይሆን ይዞታው የላሊበላን መስቀል ይመስላል ።

ከነዚህ ከጠቀስኳቸው ሁለት መስቀሎች ሌላ በገዳሙ እቃቤት ውስጥ የሚገኙ መስቀሎች በጠቅላላ ከአፄ ዮሐንስ 4ኛ ወዲህ የተሰበሰቡና ከዚያ ወዲህ በተለያዩ ግለሰቦች የተሰጡ ናቸው ።

በተለይም ከአፄ ዮሐንስ የተሰጡ ሁለት መስቀሎች ከብር ተሠርተው በወርቅ የተቀቡ ሲሆኑ በሁለቱም ገጻቸው በኩል የመላእክትና የቅዱሳን ሥዕል ተስሎባቸዋል ።

የተቀሩት የደብረ ሊባኖስ ቅርሶች ብዙ ቢሆኑም በገዳሙ እቃ ቤት ውስጥ የተለያዩ 390 ያህል መጻሕፍት ይገኛሉ ።

ግርማ ኤልያስ



www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በመንፈሳዊ አላማ

ወጣቶቻችን በሥጋዊ ድርጅቶች በ ኩል በሚያደርጉት መልካም ተሳትፎ "ትኩስ ኃይል" የሚል ቅጽል እንደተሰ ጣቸው ሁሉ በመንፈሳዊ ድርጅቶችም ውስጥ የሚታየው የወጣቶች ትብብር ና የሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ቀላል ባለመሆኑ ተስፋ የሚጣልባቸው ሆነዋል።

በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ ዋህዶ ቤተ ክርስትያን የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ሥር የሚመሩትና በየቤተ ክ ርስቲያኑ የሚገኙት መንፈሳዊያን ወጣ ቶች በሃይማኖተ አበውም ውስጥ ያሉ ት በአጠቃላይም መንፈሳዊ ፍቅር ያላ ቸው ሁሉ በመንፈሳዊ በኩል የሚያበ ረከቱትን አስተዋጽዖ ስናይ ይህ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያንን ርምጃ ያፋጥናል ብ ለን ተስፋ እናደርጋለን ። ይልቁንም የ ዛሬይቱ ቤተ ክርሳስቲያን ነገ ተተኪ ታጣ ይሆን? የሚለው ሥጋት ሊቃለል ይቻላ ል ይኸውም፡-

1. መንፈሳዊ በዓል በሚከበርበት ጊ ዜ በየቤተ ክርስቲያኑ ያሉ ወጣቶች ሴ ት ወንድ ሳይባል ከበሮ እንግበው ጸና ጽልና መቋምያ ይዘው ያሬዳዊ መዝሙ ር እየዘመሩና ወረብ እየወረቡ በደመቀ ሁኔታ ሲያሸበሽቡ ተመልካቾችን በማ ስደሰት ለበዓሉ የሚሰጡት ውበትና ድ ምቀት በጣም ከፍ ያለ ነው። በርግጥ ይ ህንን የሚያይ ሁሉ በሕፃናት አንደበት ምሥጋናን አዘጋጀህ" የሚለው ቃል ሁልጊዜ የሚሠራ መሆኑን ያስረዳል።

2. ሥጋ ወደሙን በመቀበል ረገድ ከታላላቅ ሰዎች ይልቅ ወጣቶች ቀዳ ሚ ሆነው መገኘታቸው እጅግ የሚያ ስደንቅ ነው። በተለይም በየዓመቱ በጾ መ ፍልሰታ የሚታየው የወጣቶች መ ንፈሳዊ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እጅግ የሚያስ ደስትና የሚያኮራት ነው ። በዚህ ሱባ ዔ ወቅት ወጣቶች እስከ ስምንት ሰዓት ድረስ ጦማቸውን ውለው በማስቀደስ ና ተሰጥዎ በመቀበል በመጨረሻም ቅ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል

# ክርስቲያናዊ ሕይወት

## ዕረፍት በክርስትና ሕይወት

ልዩ ልዩ ዕረፍት አለ ፤ የዕረፍት ቦታው ጊዜ ውና ስልቱ ብዙ ነው ። ማንኛውም ሠራተኛ ቀኑን በሥራ አሳልፎ ሌሊቱን ፤ ሌሊቱን በሥራ ከአሳለፈም ቀኑን በዕረፍት ያሳልፋል ።

የዕረፍቱ ሁኔታ ግን ይለያያል ፤ አንዱ መጻሕ ፍትን በማንበብና ልዩ ጥናትን በመከታተል የዕረፍት ጊዜውን ሲያሳልፍ ፤ ሌላው በመና ፈሻ ስፍራዎች በመዝናናት ጊዜውን ይጠቀም በታል ፤ ሦስተኛው ደግሞ የዕረፍትን ስልት ባለ መረዳት በመጠጥና በዕንቅልፍ ብቻ ያባክነ ዋል ። ዕንቅልፍ ለሰው ሁሉ አስፈላጊ ነው ፤ ግን በተወሰነ ሰዓት መሆን አለበት ፤ አንድ ሰው በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ስምንት ሰዓት ሰርቶ ቀሪውን አሥራ ስድስት ሰዓት በዕንቅልፍ ብቻ ላሳልፈው የሚል ከሆነ ስንፍና ነው ።

የተወሰነ ሰዓት ሠርቶ የተወሰነ ሰዓት ማረፍ ሥጋዊ ዕረፍት ነው ፤ ይህ ለሁሉም ሰው አስፈ ላጊ ነው ፤ በክርስትና ሕይወት ግን ከዚህ ተጨ ማሪ ሌላ ዕረፍት አለ ። እርሱም ከሥጋ ድካማ ነት የተነሣ ከሚመጣ ልዩ ልዩ የመንፈስ ድካም ለ ማረፍ የሚደረግ ዕረፍት ነው ። እንዲህ ዓይነቱ ዕ ረፍት የሚገኘው የት ነው? የተወሰነ ጊዜና ቦታ ስ አለው ወይ? የሚል ጥያቄ ይመጣ ይሆናል ለዚህ መልስ የሚከተለውን እንመልከት ። "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ፤ ከእኔም ተማሩ ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላ ችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና" ማቴ.11 ፡ 28 ።

በሥጋ ደካማነት የሚፈጸም ክፉ ሥራ ሁሉ የነፍስ ሸክም ነው ፤ የሕሊና ወቀሳን ያመጣል የመንፈስ ዕረፍት ያሳጣል ፤ ታዲያ የነፍስ ሸክ ም የሆነውን አውርዶ ብመጣል ከሕሊና ወቀሳ ለመዳን የመንፈስ ዕረፍት ለማግኘት "እናንተ ሸ ክማችሁ የከበደ ደካሞች ወደ እኔ ኑ እኔም አሳር ፋችኋለሁ" የሚለውን አምላካዊ ጥሪ ዛሬውኑ መቀበል ያስፈልጋል ። ይህ ዕረፍት ሥጋዊና መንፈሳዊ ዕረፍት ነው ማለት ይቻላል ምክን ያቱም የሕሊና ወቀሳ ካለ መልካም እንቅልፍ እንኳን መተኛት አይቻልም መልካም ዕንቅልፍ ከሌለ ደግሞ ዕረፍተ ሥጋ የለም ማለት ነው ።

ዕውነተኛ ዕረፍትን ለማግኘት 1ኛ የሕሊና ወቀሳ ከሚያመጣ ሥራ መራቅ 2ኛ የሰው ሕሊ ና የሚያርፍበት ጽኑዕ ተስፋ መኖር አለበት ፤ ተስፋ የምናደርገውም ከሞት በኋላ ያለው ዘለ ዓለማዊ ሕይወት ነው ፤ ያም ሕይወት "ትን ሣኤም ሕይወትም እኔ ነኝ" ያለውና "ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ" የሚለን ክርስቶስ ነው ።

የክርስትና ሕይወትም አላማው ዘላለማዊውን ዕረፍት ለመውረስ ነው ያን ዘለዓለማዊ ዕረፍት ለመውረስ ደግሞ በዚህ በአለንበት ዓለመ ሥጋ የሕሊና ዕረፍት የሚገኝበትን መልካም ሥራ ሁሉ አዘውትሮ መሥራት ያስፈልጋል ፤ ሳይ ሠሩ ዕረፍት የለምና ክርስቶስ ዕረፍታችንና ሰላማችን ነው በክርስቶስ ያመነ ወንጌልን የተ ቀበለ ሁሉ ዕረፍትና ሰላም አለው ፤ እምነት የሚገለጠው በሥራ ነው ዕረፍትም ከሥራ በኋላ እንደሆነ ግልጥ ነው ።

ስለዚህ ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም የሚያደር ጉት ዕረፍት በዕንቅልፍና በመዝናናት ብቻ መፈጸም የለበትም ፤ ከዕረፍት ሰዓታቸው በር ከት ያለውን ጊዜ ያዘኑትን ለማጽናናት የተጣሉ ትን ለማስታረቅ ፤ የታመሙትን ለመጠየቅና የተቸገሩትን ለመርዳት በመውጣት በመውረድ ማሳለፍ ክርስቲያናዊ ዕረፍት ነው ። ከአዘኑት ጋር ክርስቶስ አለ ፤ ከታመሙትና ከተቸገሩትም ጋር እርሱ አለ የተጣሉትም በታረቁ ጊዜ ፍቅር ክርስቶስ በመካከላቸው ይገኛል ፤ "ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ" የሚለንን ክርስቶስን የምናገኘው መልካሙን ሥራ ሁሉ አብዝቶ በመሥራት ነው ።

ክርስቶስ በሥጋ ወደ እኛ መጣ ፤ ለምን? እኛን ከድካመ ሥጋ ከድካመ ነፍስ ለማሳረፍ ዕረፍትን ለማግኘት እኛም ወደ እኛ የመጣውን እርሱን በእምነት መቀበል ፤ በሥራ መምሰል አለብን ፤ በእምነት ካልተቀበልነውና በሥራ ካልመሰልነው የእርሱ መምጣት ብቻ ዕረፍት ሊሆነን አይችልም ፤ ስለሆነም "ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ" ይለናል ። "የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉ ትም ለተቀበሉትና በስሙ ለሚያምኑት ለእነ ርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥል ጣንን ሰጣቸው" ስለዚህ እኛም የእርሱ ልጆች ሆነን መንፈሳዊ ሥልጣንን ይሰጠን ዘንድ እር ሱን በሥራ እንምሰለው ።

ራደ አስረስ



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሠማሩ ካህናት በቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን እህል ውኃና የደጀ ሰላምን መክፈልት ተስፋ አድር ገው ከመኖር በስተቀር ሠርተው የመጠቀም ልምድ ያላቸው የማይመስላቸው ግለሰቦች በጥ ቂቱ የሚገመቱ አይደሉም ።

አለበት ። ካህናት በሥራ በኩል ምን ያህል ተሳ ትፎ እንዳላቸው ለማመልከት በገነተ ጽጌ ቅዱ ስ ጊዮርጊስ አካባቢ የሚገኙት ካህናት ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጋር ደርበው ምን ዓይ ነት ሥራ እንደሚሠሩ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮ ርጊስ የተቋቋመው ተግባረ እድ ዋና ሥራ አስኪ



ዐይነ ሥውሩ ምንጣፍ ሲሠራ

ይሁን እንጂ ካህናት ቤተ ክርስቲያንን ከማገ ልገላቸውም በላይ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሠማርተው ከፍ ያለ ሥራ እንደሚሠሩና ማንኛ ውም ሥራ እንደማያቅታቸው የታወቀ ነው ። እንዲያውስ "ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥ ረት ድንኳን እየሠራን እንኖር ነበር" 2. ተሰ. 3 ፡ 8 እያሉ ሰው ሁሉ በሥራ እንዲጠቀምና ሥራ ለሰው ልጅ የደም ሥር መሆኑን ሲያስተ ምሩ የኖሩና አሁንም የሚያስተምሩ ካህናት አይደሉምን?

ዛሬም በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ተሠማርተው ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጋር ድርብ ሥራ መሥራት የሚገኙት ካህናት መሆናቸው መታወቅ

ያጅ መምሬ አየለ በቀለን ጠይቀናቸዋል ።

ትንሣኤ ፡- መምሬ አየለ በቀለ ይህ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ የተቋቋመው የተግባረ እድ ሥራ ስንት ዓመት ይሆነዋል?

መ.አ. ፡ ይህ ተግባረ እድ አሁን በቅርብ ጊዜ ማለት የካቲት 13 ቀን 71 ዓ.ም. ነው ሥራውን የጀመረው ስለዚህ 7ኛ ወሩ ነው ።

ትንሣኤ ፡- ሥራው የተቋቋመ በተለያዩ ግለሰ ቦች ነው? ወይስ በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ይህ ንን ቢያብራሩልኝ?

መ.አ. ፡- ሥራው የተቋቋመው በተለያዩ ግለ ሰ ቦች ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ነው ሊቋ ቋም የቻለ ።

ትንሣኤ ፡- በዚህ በሥጋጃ የሚሠሩት ሠራተኞች በቀዋሚነት ነው? ወይስ በቀን ሠራተኛነት የሚሠሩት?

መ. አ. ፡- ሠራተኞቹ በቀዋሚ ሠራተኛነት ነው የሚሠሩት ይኸውም በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ስለሆኑና ይህንን ሥራ ደግሞ ደርበው ስለሚ ሠሩት ለጊዜው ደመወዛቸው የሚያገኙት ከቤተ ክርስቲያን ነው ለደወፊት ግን ማለት ከመስከ ረም 1 ቀን 72 ዓ.ም. ጀምሮ ደመወዛቸው እንዲ ሻሻልላቸው ታስቧል ።

ትንሣኤ ፡- መምሬ አየለ ለመሆኑ ከዚህ ውስጥ የሚሠሩት ሠራተኞች ስንት ይሆናሉ? ብዛታቸ ውና ከየት ከየት እንደመጡም ቢገልጹልኝ?

መ.አ. እነዚህ የሚያዩዋቸው ሠራተኞች ከሌላ የመጡ አይደሉም ከዚህ ከገነተ ጽጌ ቅ.ጊዮር ጊስ አካባቢ የሚኖሩ ቤተ ክርስቲያንንም የሚ ያገለግሉ ቀሳውስትና ዲያቆናት መነኮሳት መዘ ምራን እንዲሁም ዘበኞች ማለት የቤተ ክርስቲ ያኑ አገልጋዮች ናቸው ። ብዛታቸው ስንት ይሆ ናሉ ስለሚሉት ግን የሠራተኞቹ ብዛት መቶ አሥር ነው ይሁን እንጂ ከእነዚህ ውስጥ ባጀት ያላ ቸው 96 ሲሆኑ የቀሩት ግን ባጀት የላቸውም ።

ትንሣኤ ፡- መምሬ አየለ የሠራተኞቹ ብዛት መቶ አሥር ነው ግን ከእነዚህ ውስጥ 96ቱ ባጀት ሲኖራቸው ሌሎቹ ባጀት የላቸውም ብለ ዋል ታድያ እነዚህ 14ቱ ሠራተኞች በምን ይተዳደራሉ?

መ.አ. ፡- ሌሎቹ ባጀት የላቸውም የተባሉት ከውጭ የመጡናቸው ይኸውም ለመማርና ሥራ ውን በሚገባ ለማጥናት እንጂ በቀዋሚ ሠራተኛነ ት የተቀጠሩ አይደሉም ይሁን እንጂ ሥራውን በደ ምብ ካጠናቀቁ በኋላ የምስክር ወረቀት አግኝተው እንደሌሎቹ ጓደኞቻቸው በበጀት ይደለደላሉ በዚ ህ አሁን ባሉበት ተወስነው የሚቀሩ አይደሉም።

ትንሣኤ ፡- እነዚህ ሰዎች ከዚሁ ድርጅት ትምህር ታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወዴት ይሄዳሉ? ቤተ ክህነት ትቀበላቸዋለች? ወይስ እነሱ ወደ ፈለጉበት ነው የሚሄዱት?

መ.አ. ፡- እነዚህ በመማር ላይ ያሉት ሠራተኞ ች ይህንን የተግባረ እድን ትምህርት በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ የትም ወድቀው አይቀሩም ቤተ ክህነት ትቀበላቸዋለች ከዚህም ሊቀጠሩ ይች ላሉ ምክንያቱም ሥራው ብዙ ነው 12 ዓይነት የሥራ ዘርፍ ስላለው ከዚህ ሊቀጠሩ ይችላሉ ።

የሥራው ዓይነት 12 ነው ያልኩትም ፡-

1ኛ ስጋጃ
2ኛ የሽመና ሥራ
3ኛ ብሩሽ
4ኛ ቦርሳ
5ኛ የልብስ መያዣ የቆዳ ሥራ



www.ethiopianorthodox.org

6ኛ የቃጫ ቦርሳ
7ኛ ከጠጉር የሚሠራ የቢሮ ምንጣፍ ወዘተ የመሳሰሉት ስለሆኑ ለወደፊት ብዙ ሰው ሳያስ ፈልገን አይቀርም ማለቴ ነው ።

<u>ትንግኢ</u> ፦ መምህር አየለ ከምርቱ የሚገኘው

በደምብ አሠራሩን እንዲይዙት አስተምራቸዋለሁ ።

## የቀለሞቹ አሠራር

1ኛ ቀይ ቀለም ለመሥራት ስንፈልግ ከቀይ አፈር አምጥተን ሰልቀን እናቦካዋለን ደህና



ካህናቱ ከቃጫ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ይሠራሉ

ገቢ ለምን እንደሚውል ሰፋ አድርገው ቢያብራሩልኝ ?

<u>መ.አ.</u> ፦ ከምርቱ የሚገኘው ገቢ በቤተ ክርስ ቲያን ይሰበሰብና ከተሰበሰበ በኋላ ከመላ ጉደል ቤተ ክርስቲያኑን ለሚያገለግሉና ከዚህ ለሚ ሠሩ ሠራተኞች ይመወዝ ይውላል ሥራው የተ ቋቋመው ለዚሁ ነው ።

<u>ትንግኢ</u> ፦ ሥራው ለወደፊት ያለው ዕቅድ እንዴት ነው ?

<u>መ.አ.</u> ፦ የወደፊት ዕቅዳችን ሰፊ ነው ይኸውም ዕቅዳችን በዚህ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮር ጊስ የሚገኙት ቀሳውስትና ዲያቆናት መዘምራን ሁሉ የሰውን እጅ ከመመልከት ድነው ራሳቸውን በራሳቸው ረድተው እንዲኖሩና ከች ግር ነጻ እንዲሆኑ ከዚህም ሌላ እየተመጻወቱ ከመኖር ይልቅ እነሱ ለተቸገረ ሁሉ እንዲመጸ ውቱ ነው ከዚህ ውስጥ የሚሠሩት ሥራዎች ስጋጃ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ ሥራዎች ማለት አበባ ምንጣፍ የመሳሰሉት ጭምር ስለሚሠሩ ቤተ ክርስቲያንዋ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ካለባት ችግር እንደምትላቀቅና ከፍ ያለ ገቢ ምንጭ መደ ብር እንደምትሆን አንጠራጠርም ዋና ዕቅዳች ንም ይኸው ነው እያንዳንዱ ሰው ችግሩን ራሱ እንዲወጣውና ችግሩን ራሱ በሥራ እንዲያስ ወግደው ነው ።

ከዚህም አያይዤ የማላልፈው ቢኖር ቀለም አልቸገርም ራሴ አዘጋጄለሁ የተለያዩ ቀለሞ ችንም አቀርባለሁ ይኸውም 12 ዓይነት ቀለም አለኝ ይህንንም ሠራተኞቹ እንዲያውቁትና

ሁና ከቦካ በኋላ ጨው ፣ ስኳር ፣ ዘይት እንጨም ርበታለን ይኸውም ከቀይ አፈሩ ላይ የሚጨ መረው ስኳሩ እንዲያያይዘው ፦ ጨው እንዲያ ዋህደውና እንዲያብላላው ፣ ዘይቱ ደግሞ እንዲ ያለሰልሰው ነው ። 2ኛ አረንጓዴ ቀለም በምን

ጊዜ ደምበኛ አረንጓዴ ቀለም ይሆናል ።

3ኛ ብጫ ቀለም ደግሞ ስንፈልግ የመቅመቆ ሥር ምስን በጥሩ ሁኔታ አፈሩን አስለቅቀን እንከትፈውና እናደርቀዋለን ከደረቀ በኋላ ይደቆሳል ልሞ ከተደቆሰ በኋላ ተሰልቆ ለተወሰነ ጊዜ ተቦክቶ ይሰነብታል

ከዚህ በኋላ እሱም እንደ ሌሎቹ ቀለሞች ጨው ስኳር ፣ ዘይት ሲጨመርበት ጥሩ ብጫ ቀለም ይሆናል ።

4ኛ ሰማያዊ ቀለም ስንፈልግ ደግሞ የበሰሉ የአጋም ፣ የጠምበለልና የዶቅማ ፍራፍሬዎችን

ለቅመን ሁሉንም አንድ ላይ እን ፈጫቸዋለን ከተፈጨም በኋላ ከአንድ ንጹሕ ዕቃ ይቦካና እነዚያን ሦስት ቅመሞች ማለት ጨው ፣ ስኳርና ዘይት ጨምረን እንጠቀምበታለን ፤

5ኛ ለብርቱካን ቀለም ደግሞ የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች የቱልትና የመቅመቆ ሥር ምስን ቅርፊቱን እንፍቅና ከትፈን እናደርቀዋለን ፈጭተንና አብኩተን በጨው በስኳርና በዘይት ከተቀመመ በኋላ ግሩም ቀለም ይሆናል ።

6ኛ እንደዚሁም ሁሉ ጥቁር ቀለም በምንሠራበት ጊዜ አስቀድመን ጥላሸት እንሰበስባለን እንክርዳዱንም አሳርረን ቆልተን በውኃ እንዘፈዝፈዋለን ከዚህ በኋላ እንክርዳዱ በተዘፈዘፈበት ውኃ ጥላሸቱን እናሸዋለን ከዚህም ጋር ከላይ የተጠቀሱት ዘይት ፣ ጨውና ስኳር ሲጨመርበት ግሩም የሆነ ጥቁር ቀለም ይሆናል ሌላ ቀርቶ መጻፍም ሊጻፍበት ይችላል ።



በልዩ ልዩ ተግባረ እድ ላይ ሳሉ

ፈልግበትም ወቅት ከዕፀዋት ማለት ከዶቅማ ቅጠል ከጌሾ ፣ ከጠምበለል ከአጋም ቅጠላቸው በደምብ ይወቀጡና ሁሉም አንድ ላይ ተደባልቀው ይቦካሉ የቦካው በደምብ ከተብላላ በኋላ ጨው ስኳርና ዘይት እንጨምርበታለንበዚህ

7ኛ ነጭ ቀለምም ስንፈልግ ነጩን አፈር ከአንዳንድ ማዕድን ፈልገን አምጥተን አልመን እንፈጨውና ጥሩ ሁኖ ከቦካ በኋላ ጨው ስኳርና ዘይት ይጨመርበታል ከዚህ በኋላ ለስዕል ለጠመኔ ለሌላም ነገር ደህና ሁኖ ያገለግላል ።



8ኛ ከዚህም ሌላ ቡና ዓይነት ቀለም ስንፈልግ ቀዩ ቀለምና ጥቁሩን ቀለም በትክክል በሚዛናዊ አሠራር ስናዋህደው ወደ ቀይነትም ወደ ጥቁርነትም ሳያዘነብል ቡናማ ዓይነት ቀለም ይሆናል በዚሁ እንጠቀማለን ።

9ኛ ሐምራዊ ቀለምም የጽጌረዳ አበባዎች ከላይ በተጠቀሱ ቅመሞች ቀምመን እንሠራለን ከመላ ጉደል በዚህ ዓይነት አሠራር ነው ስንጠቀም የምንኖረው ።

<u>ትንግኢ</u> ፦ መምሬ አየለ የምትሠሩት ዕቃ ሁሉ ይሸጥላችኋል ?

<u>መ.አ.</u> ፦ ስንኳንስ ተሠርቶ ገዥ አጥቶ ሊቀመጥ እስኪሠራ ድረስ እንኳን መቼ ነው የምታደርሱልን እያሉ የሚያስቸግሩን እጅግ ብዙ ናቸው እንዲያውም ለሌላ እንዳይሸጥባቸው አስቀድመው ነው ቀብድ የሚሰጡን ።

<u>ትንግኢ</u> ፦ መምህር አየለ ይህንን ሥራ ስታቋቁሙት ያጋጠማችሁ ችግር እንዳለ ቢገልጹልኝ?

<u>መ.አ.</u> ፦ ሥራው ሲቋቋም በጣም ችግር አጋጥሞን ነበር ያጋጠመንም ችግር ሥራው ከተቋቋመ ከየካቲት 13/71 እስከ ግንቦት 30 ቀን 71 ዓ.ም. ድረስ ገብ ታቸው ይሁን ሳይገባቸው እኔ አላውቅም ካህናቱ አስቸግረውን ነበር ዛሬ ግን በእውነቱ ከሰኔ ወር ጀምሮ ሥራው መልካም መሆኑን ስለተገነዘቡ በሥራው ተሳታፊዎች ሁነው ይገኛሉ ።

<u>ትንግኢ</u> ፦ ይህንን ድርጅት ቤተ ክህነት ያውቀዋል አያውቀውም ?

<u>መ.አ.</u> ፦ ቤተ ክህነት ያውቀዋል እንዲያውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በቅርብ ተመልክተውት በሥራው ስለ ተደሰቱበትና ለወደፊቱም ከፍ ያለ ምርት የሚያስገኝ መሆኑን አምነውበት የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ሥራ አስኪያጅ እንዲተባበሩን በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ለሥራማስኪያጅያ የሚሆን ብር 3374.50 ወጭሁና እንዲሰጥ አዝዘዋል ምንም እንኳ እስከ ዛሬ ድረስ በእጃችን ባይገባም ይህ የታዘዘልን ገንዘብ በቅርብ ጊዜ ይደርሰናል ብለን በመጠባበቅ ላይ ነን ሲሉ ገልጸውልናል ።

<u>ከአዘጋጁ</u> ፦ ተግባረ እድ ለካህናት እንግዳ ነገር አይደለም ቀድሞ ብራናእየዳመጡ ቀለምእያወጡ መጻሕፍትን በስዕልና በተለያዩ ሐረጎች እያስጌጡ ሲሠሩ የነበሩት ካህናት መሆናቸው ግልጽ ነው ።

ዛሬም ቢሆን ሥራቸውን በማሻሻል በተለያዩ የተግባረ እድ ሥራዎች ተሰማርተው ሲሠሩ ይታያሉ ። በእውነቱ ካህናት በያዙት ጥበብ እየተጠቀሙ በየቤቱ ክርስቲያኑ የጎጆ እንዱስትሪ ቢያቋቁሙ ከራሳቸው አልፈው ሌላውንም ለመርዳት እንደሚችሉ አንጠራጠርም ።

ከንፈርግብ ማርቆስ

## ወጣቶች በመንፈሳዊ...

ከገጽ ፲፬ የዞረ

ዱስ ቁርባኑን ለመቀበል የሚያደርጉት እሽቅድምድም እጅግ የሚደነቅ ነው ።

ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 16 ቀን 1971 ዓ.ም በ42 አብያተ ክርስቲያናት እየተ ዘዋወረ ሰበካ ጉባኤን ሲያጠናክርና ስብከተ ወንጌልንም ሲያስፋፋ የቆየው የሁለተኛው ዙር አጠናካሪ ቡድን ውስጥ ተመድበው የስብከተ ወንጌልን ሥራ ሲያስፋፉ የቆዩት ሰባክያን እንዳስረዱንና እኛም በተመደብንበት ሥፍራ ሁሉ በዓይናችን እንዳየነውና እንደተረዳነው ሁሉ ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል በየቤተ ክርስቲያኑ በሰልፍ የሚቀርቡት ወጣቶች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ እንደነበረ ለመረዳት ችለናል ።

ለማስረጃ ያህል በተለይ በማኅደረ ስብሐት ልደታ ቤተ ክርስቲያን ያየነውን ለመግለጥ ብንሞክር የሌላውንም አጠቃላይ ግምት ለመውሰድ ይረዳል ብለን እናምናለን ።

በማኅደረ ስብሐት ልደታ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበሉት ወጣቶች ቁጥር በጣም ብዙ ስለነበር የቅዱስ ቁርባን አቀባበል ሥርዓት በልዩ ፕሮግራም ይካሄድ ነበር ። በዚህም መሠረት ሴቶችና ወንዶች ወጣቶች ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት እለታት ተራቸውን ጠብቀው የሚቀበሉ ሲሆን ሕፃናት ቅዳሜና እሁድ ፤ አዋቂዎች ደግሞ እንደ ደብረ ታቦር ባሉት ታላላቅ በዓላት እንዲቀበሉ በፕሮግራም ስለወጣ ሥነ ሥርዓቱ በዚሁ ቀጥሎ ሲካሄድ ቆይቷል ። ሥጋ ወደሙን የመቀበሉ ሥነ ሥርዓት የሚካሄደው በምዕራብና በምሥራቅ በሁለት ቦታ ነበር ። ይህም ሆኖ በተለይ በሴቶች ወጣቶች ተራ ጊዜ ከ45 ደቂቃ በላይ በመቀበል ብቻ እንደሚቆዩ ተመልክተናል ይህም ሊሆን የቻለው ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበሉት ወጣቶች ቁጥር በጣም ብዙ በመሆኑ ነው ።

ለምሳሌ በአንድ ቀን ቅዱስ ቁርባን የተቀበሉት ሴቶች ወጣቶች ከፍተኛ ቁጥር 1800 ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 1000 ነው ።የወንዶች ወጣቶችም ከፍተኛ ቁጥር እስከ 900 እንደነበርም ሁኔታውን በቅርብ ሆነን ከመመልከታችንም በላይ የሚመለከታቸውም ክፍሎች ይህንኑ አረጋግጠውልናል ። እንግዲህ ይህ ከሰባት ዓመት በላይ ያሉትን ወጣቶች ብቻ እንጂ ሕፃናትንና አዛውንትን አያጠቃልልም ታዲያ በ16 ቀን ውስጥ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የቁረቡት ወጣቶች ቁጥር ብዛቱን ለማወቅ በማዕከላዊ ቁጥር አባዝተን ብናይ ውጤቱ ምን ያህል እንደሆነ ለመተመን እንችላለን ከዚህም ጋር በአዲስ አበባው ስጥ ባሉት 42 አብያተ ክርስትያናትም ምን ያህል ወጣቶች ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል እንደቻሉ የተወሰነ ቁጥር መናገር ባይቻልም ብዛቱን መገምገም ቀላል ነው ይህንን ለማተት የፈለግነው በቤተ ክርስቲያን የወጣቱ ተሳትፎ ምን ያህል እንደሆነ ለመግለጥ ነው። በዚህም አንፃር ሥጋወደሙን ለመቀበል የሚቀርቡት አዛውንት ብዛት ከዚህ ጋር ሲመጣጠን በጣም አነስተኛ መሆኑ አዛውንቶች ከቅዱስ ቁርባን ምን ያህል እንደራቁ ለመገንዘብ ይቻላል ። ግን እስከመቼ? "ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" የሚለው አምላካዊ ቃል የተነገረው ለሕፃናትና ለወጣቶች ብቻ ስላልሆነ በእድሜ ወሰን ሳንከለል እያንዳንዳችን ንስሐ እየገባን ሁል ጊዜ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ዝግጅዎች መሆን አለብን ያም ሆነ ይህ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የወጣቶችን መንፈሳዊእንቅስቃሴና ትጋት ለመግለጥና እነሱንም ለማነቃቃት ስለሆነ አሁንም በርቱ እንላቸዋለን ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ



www.ethiopianorthodox.org

# የጤና ዓምድ

## የካንሰር በሽታ

በዚህ የጤና አምድ ዝግጅታችን ካንሰር ወይም ነቀርሳ ስለተባለው በሽታ መነሻ ምልክትና መከላከያውን በሚመለከት ሁኔታ የደስታና የጤና ጕዳና ከተሰኘው መጽሐፍ ለአንባብያን እናቀርባለን ። ሁላችንም እንደምናውቀው ደስታ የሚገኘው አካላችን ሙሉ በሙሉ በጤና የተጐናፀፈ እንደሆነ ነው በጤና ጉድለት ምክንያት ከሰውነታችን ክፍል አንደኛውን በሽታ ቢይዘው ጠንቁ ለመላ አካል ክፍላችን ስለሆነ በጤና ከምናገኘው ደስታ ርቀን ትርፋችን ጭንቀትንና በሽታን ማስታመም ይሆናል ። እግዚአብሐሔር በአስደናቂ ሁኔታ የፈጠረልንን ሰውነታችንን ብንከባከበው ለበሽታም ከሚያጋልጡት ነገሮች ብንጠብቀው የሙሉ ጤንነት ባለቤቶች መሆን እንችላለን በዚያው አንጻር ስለሰውነታችን ጤንነት ግድ ባይኖረን ሰውነታችንን ለልዩ ልዩ በሽታዎች እናስረክበዋለን ።

የሚይዙን በሽታዎች ሁሉ ያለ አንዳች ምክንያት አይመጡም ለሰውነታችን ከምናደርግለት የጤና አጠባበቅ ጉድለት የተነሳ የበሽታዎች ሁሉ ማኅደር እንሆናለን ከዚህም ሌላ የበሽታው መነሻና ምልክት ምን እንደሆነ ለይተን ስለማናውቀው ያለምንም የሐኪም ርዳታ ብቻችንን ሲያሰቃየን ከቆየ በኋላ በሽታው ተስፋፍቶ አስጊ ደረጃ ላይ ሲደርስ ወይም ብሶብን በሞትና በሕይወት መካከል ስንሆን ወደ ሆስፒታል እንሄዳለን እንደጀመረን የሐኪም ርዳታ ብናደርግ የሚተወን በሽታ እስከሞት ያደርሳል ወይም የማይድን ሊሆን ይችላል ገና በሽታ እንደጀመረ መታከምና በሽታው በሰውነታችን ከተዋሐደ በኋላ መታከም የተለያየ ስለሆነ ለመዳን የሚችለውን በሽታ ከሰውነታችን እናቆራኘዋለን ይህም ለጤናችን ያለመጠንቀቃችንን ያመለክታል በዚሁ ከጥንቃቄ ጉድለትና ቶሎ ሄዶ ካለመታከም ጠንቅ ከሚነሱት በሽታዎች አንዱ ካንሰር ወይም ነቀርሳ እየተባለ የሚታወቀው በሽታ ነው በሽታው እንኳን በሰውነታችን እንዲኖር ይቅርና ስሙ እንኳን ሲጠራ የሚዘገንን ነው ካንሰር በእርግጥ አደገኛ በሽታ ነው እንዳይዘን ከመጠንቀቅ በስተቀር በሕክምና የተሳካ ውጤት እምብዛም አያገኝምና በበሽታው የተያዘ ሰው ከመከላከል በስተቀር የሚበጀው የለም ሐኪሞች አሁንም ስለበሽታው በማጥናት ላይ ቢሆኑም ለመነሻዎቹና ለመከላከያው የሚሆኑትን እንደደረሱበት ከሆነ ሲጋራ ማጤስ የበሽታው መነሻ ሊሆን መቻሉ ነው ። ለመከላከል መነሻው ከታወቀ ማጤስን መተው ነው ። ከዚህም ሌላ በሽታው ተላላፊ ስለሆነ በተጋቦት በቀላሉ ሌላውን ሊይዝ ይችላል ። ብዙውን ጊዜ በሰውነታችን የሚመጣብንን በሽታ እንዲያው ሲያመን ከማወቅ በስተቀር የምን በሽታ ምልክት እንደሆነ የምንሰጠው አስተያየት በዘልማድ ስለሆነ ለበሽታው ምቹ የመስፋፊያ ጊዜ እንሰጠዋለንና በሰውነታችን ይንሰራፋል።

ሳብዙ ጊዜ ያለመከላከያ በሰውነታችን መኖር የተለማመደ በሽታ ምንም ዓይነት ሕክምና ቢደረግለት ፈውስን ላያገኝ ይችላል ።

ለምሳሌ ፣ ካንሰር አደገኛ በሽታ መሆኑን የምናውቀው በሽታው በውስጣችን አድሮ ሲያሰቃየን ብቻ ነው ነገር ግን ማንኛውም በሽታ ከሚደርስብን በፊት የጤና አጠባበቅ የሚመለከቱትን መጽሐፎች በማንበብና ሐኪሞችን በማማከር መረዳትና መጠንቀቅ እንችላለን ። በሽታው ካሳየው ልዩ ልዩ ምልክት ቀጥሎ ዋነኛው ደረጃ ከመድረሱ በፊት የሚያሳየው ምን ምን ሁኔታ እንደሆነ እንመልከት ።

የካንሰር በሽታ ምልክት

እባጭ ሆኖ በሰውነታችን ሲወጣ ፣

ክብደትን ለመቀነስ ከሚደረጉ ሁኔታዎች፣

የማይድን ዓይነት ቁስል ሆኖ በሰውነት ሲወጣ ፣

የተለመደ የሆድ ቁርጠት ወይም የአመጋገብ ችግር ፣

ምግብ ሲውጡ መቸገር ፣

የድምፅ ቃና መለወጥ ወይም መሻከር ከጉሮሮ ውስጥ ቁስል መውጣቱን ያመለክታል ። የማይድን ዓይነት ሳል (እስከ ሁለት ሳምንት ካልዳነ) እነዚህ ምልክቶች የሳንባ ነቀርሳ (የካንሰር) በሽታ መጀመሪያዎች ናቸው ተብለው ተጠቅሰዋል ። መድኃኒቱ ከእነዚህ ምልክቶች አንዱ እንኳ በሰውነታችን ከታየ በፍጥነት ወደሐኪም ሄዶ መማከር ያስፈልጋል የበሽታው አጥቂነት የሳንባን ክፍልና የውስጥ ሰውነትን ማቁ ሰል ነው ይኸ የመጨረሻው አደገኛ ደረጃ ነው ማለት ነው ። ከዚህም ደረጃ ላይ ቢደርስ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን የሐኪም ዕርዳታ መጠየቅ አይከፋም ።

ከዚህ በተረፈ በሽታው ከአንዱ ወደሌላው በቀላሉ ሁኔታ በትንፋሽ እንኳ ሳይቀር ይተላለፋል ለመጠንቀቅ እንኳ ሁልጊዜ የተሳካ አይሆንምና በአንዱ ሰው ምክንያት ብዙዎች በበሽታዎች ይመረዛሉ እግዚአብሐሔር ጤናና ደስታ እንድናገኝ ይፈቅዳል ። በሽታም በውስጣችን እንዲኖር ፈቃዱ አይደለም ዳዊት በመዝሙሩ አቤቱ በአንተ ግሩም ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ይላል እኛም ከእግዚአብሐሔር የተሰጠንን ሙሉ ጤናችንን ብንጠብቅ በጤናችን ሆነን የእግዚአብሐሔርን ግሩም ድንቅ ሥራ እንደ ዳዊት ማወቅ እንችላለን ።

ወዳጄ ሆይ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንደሚከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እመኝልሃለሁ ።

ወ ት ንብረት አበበ





# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

ከእጅጉ ረታ

በቁጥር 23 ትንሣኤ መጽሔት ላይ ጾም በጥንቱ የአሕዛብ ዓለም የነበረው ስፍራ ምን መሆኑን ለመግለጥ ሞክሬአለሁ። ቀጥሎም ስለ ዕብራውያን ጾም ከብሉይ ኪዳንና ከሥርዓተ ረበናት ከታሪክም የተገኘውን በማቀነባበር ማቅረቤ ይታወሳል። በዛሬው ጽሑፍ የማቀርበውም ጾም በክርስትና እምነት ውስጥ ያለውን ስፍራ ባጭሩ ለማመልከት ነው።

ያለፉት ሁለት ጽሑፎችም ሆኑ ይህ ጽሑፍ የሚያወሱት ስለጾም አጀማመርና ጾም ለመጾም ምክንያት የሆኑት ነገሮች ምን መሆናቸውን ለማመልከት መሆኑ ግልጽ ነው። ታዲያ "ይህን ያውቃሉን ? በሚለው ርእስ መውጣት ነበረባቸው ወይ? የሚል ጥያቄ ቢነሳስ? እዚህ ላይ ጥያቄውን ላቀየውና ለመሆኑ ጾም ከመንፈሳዊ ዓለም ክልል ውጭ ያለውን ይዘት ያውቃሉ ? በአካላችንና በጤናችን ላይ ያለው ይዘትስ ምንድን ነው? እንግዲህ ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት የተንሳሳሁበት ዋና ምክንያት ይህ መሆኑን በቅድሚያ ይረዱልኝ።

ታድያ ቀድሞውኑ እነሳሴ ይህን ለማቅረብ ሆኖ ሳለ ፣ በቀጥታ ወደዚሁ ውስጥ ዘው ብዬ መግባቱ ደስ አልልህ ስላለኝ ነው ጾም በሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ይዘት በአንጻሩ ለማሳየት የተገደድኩት ።

እዚህ ላይ ወደ ዋናው ቁም ነገር ልመለስና ጾም በክርስትና እምነት ውስጥ ያለው ስፍራ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተመለከተው እምብዛም የተለየ አይደለም።

በዚህ ረገድ ብዙ ሁኔታዎችን ማነጻጸር ይቻላል ። ባጭሩ ግን ሙሴ 40 ቀንና 40 ሌሊት እንደ ጾመ ጌታም 40 ቀንና ሌሊት መጾሙን ብቻ መጥቀሱ ይበቃኛመሰለኝ ።

መድኃኔታችን በዚህ ምድር ላይ በቆየበት ጊዜ የዕብራውያንን ሕግና ሥርዓት ያከብር እንደነበር ወንጌላዊያን ጽፈዋል። ይህ ከሆነም በአሪቱ የታዘዘውንም ሆነ በረበናት የተደነገጉትን አጽዋማት ጌታ ጾሞአል። ነገር ግን ጸሐፍት ፈሪሳውያን በሚጾሙበት ጊዜ በሰው ፊት ጻድቃን መስለው ለመታየት ሰውነታቸውን ያጠወልጉና ያጐሰቁሉ ስለነበር ግብዝነታቸውን አጥብቆ ነቅፎታል። የክርስትያኖች ጾም ግብዝነት ወይም መመጻደቅ የሌለበት ለታይታም መሆን እንዳይገባው አስተምሯል። ሆኖም ምን ቀን መጾምን ምን ቀን ከጥሉላት ወይም ከማናቸውም የምግብ ዓይነቶች መከልከል እንዳለብን በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አልተመለከተም። የጾሙን ወቅትና የአጿጿሙን ዓይነት ለይቶ ራሱ ጌታ በቀጥታ መስራቱን ወንጌላውያን አልጻፉልንም። ጌታ ለጾሙ የተወሰነ ሕግና ሥርዓት በቀጥታ በቃሉ ሠርቶ ባይተውልንም ፣ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ኃይልና ጥቅም የሚገኝበት መሆኑን ግን በተግባር ገልጧል። አርአያነቱንና ምሳሌነቱንም እንድንከተል መንገዱን አሳይቶናል። ጌታ የጾሙን ሕግና ሥርዓት በቀጥታ አለመሥራቱም ራሷ ቤተ ክርስቲያን ሕጉን ሥርዓቱን ወስና እንድትፈጽም ለራሷ የተወውመብትና ሥልጣን ነው ለማለት ይቻላል።

ጾም የኀዘን መግለጫ መሆኑን ከአሕዛብ ልማድ፣ ከእሥራኤል ታሪክ ጠቅሼ አመልክቼ ነበር ። በሐዲስ ኪዳንም ውስጥ ይህንኑ የሚያስረዳ እናገኛለን ። አንድ ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጌታን"… እኛና ፈሪሳውያን … የምንጦመው፣ ደቀመዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ስለምንድነው " ብለውት ነበር።ጌታም ሲመልስላቸው ሚዜዎች ሙሽራው ከእነሱ ጋር ሳለ፣ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል ፣ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ" ብሏቸዋል። ማቴ. 9 ፣ 14 ፣ 15።በዚህም ሐዋርያት ከእርሱ ጋር በነበሩባቸው አመታት አለመጾማቸው ፤ ግን ከተያዘባት ሰዓት አንስቶ ከሙታን ተለይቶ እስከተነሳባት ጊዜ ድረስ በኀዘን ተኮራምተው ከእህል ከውሃ ተከልክለው እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ፍትሐ መን. 15 ፣ 579 በሀገራችንም ከጸሎተ ሐሙስ እስከ ትንሣኤ የሚደረገው አክፍሎት ከዚሁ የመጣ ነው።

በሐዋርያት ዘመንና ከዚያም በኋላ ጾም የተከበረ ስፍራ ነበረው። በማኅበርም ሆነ በግል የሚጾምበት ጊዜ ነበር ሥርዓተ ክህነት ሲፈጸም፣ የሐዋ.ሥራ 13፡ 1-3 ሥጋውና ደሙን ለማክበር ለመቀበል ሲያስፈልግ መጾም የተለመደ ነበር ። ይልቁንም ዶመ አርብዓ የሚጾምበት አቢይ ምክንያት የትንሣኤ ዕለት ለመቁረብ ሲባል የመዘጋጃ ጊዜ መሆኑን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ ጠቅሶታል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጌታ በደማስቆ ከተገለጠለት በኋላ ሦስት ቀን ሙሉ እህል ውሃ ሳይቀምስ መጾሙን እናውቃለን የሐ.ሥ.9 ፣ ብዙ ጊዜ ይጦም እንደነበርም ራሱ ገልጧል። 2ኛ ቆሮ. 11 ፣ 27

ብቻ ያም ሆነ ይህ በ4ኛው ምዕተ ዓመት በኒቅያ የተሰበሰበው ዐቢይ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ የጾምን ሕግና ሥርዓት ወስኖ እስኪያጸና ድረስ ፡ በየሀገሩ የሚፈጸመው የጾም ሥርዓትና የሚጠበቀው የጾም ወቅት አንድ አይነት አልነበረም።

በፍትሕ መንፈሳዊ መጽሐፍ ከጾም ሁሉ የተለየ ሥፍራ የተሰጠው ለጾም 40 እና በተለይም ለሰሙነ ሕማማት ነው ። ይህ የቤተ ክርስተያን ሕግ መጽሐፍ የሰሙነ ሕማማት ዕለታት " የኀዘን ቀኖች ናቸው "ይላቸዋል። የደስታ ቀኖች ስላይደሉም "ከቂጣ ከጨውና ከውሃ በቀር ምን ምን አይብሉባቸው" ሲል ደንግጓል በተጨማሪም በጾሙም ወቅት በተድላ በደስታ ፈቃዳችንን ካደረግን ትንሣኤውን ባየን ጊዜ ተድላ ደስታችን ውዴት አለ? ሲሉ ያመለክታል፡

•ጾም ጸሎትና ምጽዋት በአንድነት መፈጸም እንዳለባቸው በማቴ. ም . 6 ቁ. 1-18 ከተጻፈው እንረዳለን።

እስከዚህ ጾም በሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ያለው ስፍራ ምን መሆኑን ባጭሩ ያመለከትሁ ይመስለኛል። በሚቀጥለው ጊዜ የጾምን ሌላውን መልኩን ማለትም ለሥጋዊ አቋማችንና ለጤንነታችን የሚሰጠውን ጥቅም ለማቅረብ እሞክራለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

# ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ

ስለ ሥነ ጽሑፍ ከመናገሬ በፊት ስለ ፊደል በአጭሩ እገልጻለሁ ፤ ለምሳሌ ሥር ከሌለ ግንድ አይኖርም ፤ ግንድም ከሌለ ፍሬ ሊገኝ አይችልም ፤ እንደዚሁም ፊደል ባይኖር ኖሮ ሥነ ጽሑፍም አይኖርም ነበር ሥነ ጽሑፍም ከሌለ በልብ የሚታሰበውን፤ አሳብ በአፍ የሚነገረውን ቃል አካላዊ በማድረግ አግዝፎ ለተተኪው ትውልድ ለማቆየት አይቻልም ፤ ስለዚህ የሥነ ጽሑፍ ዋና መዋቅሩ ፊደል መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል ።

ፊደል ሲባል በአካሉ ፤ በቅርጹ ፤ በአነጋገሩና በይዘቱ አንድ ጊዜ ተሟልቶ አልተገኘም አነጋገሩና ይዘቱ በየጊዜው በተነሡ ሊቃውንት እየተሻሻለ አሁን ከምንገኝበት ክፍለ ዘመን ደርሷል ፤ ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ፊደል ለመጀመሪያው ሥነ ጽሑፍ መሠረት ሲሆን የመጀመሪያውም ቋንቋ ለመጀመሪያው ኅብረተሰብእ መገናኛ ድልድይ ሆኖ መቆየቱ የተረጋገጠ ነው ።

እንደ አሁኑ ክፍለ ዘመን የሰው ልጆች በአእምሮ ሳይራቀቁ ፤ በዕውቀት ሳይበለጽጉ የሚናገሩትን በጽሑፍም አጉልተው በወረቀት ላይ ቀርጸው የማሳየት ልምድ አልነበራቸውም ፤ ቢሆንም በልዩ ልዩ ሥነ ፍጥረት መልክ ተቀርጸው እንደ ሥነ ጽሑፍ የሚታዩ ልዩ ልዩ ሥዕሎች ነበሯቸው ።

ወደ ሥነ ጽሑፍ መለስ ብለን ስንመለከት ደግሞ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን እናገኛለን በኢትዮጵያ ሥነ ሕጽሑፍ የተጀመረበትን ጊዜ መርምሮ ለማግኘት አያሌ ሊቃውንት በርከት ያለ ጊዜያቸውን አጥፍተዋል ፤ ነገር ግን ድካማቸውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉና የሚረዱ ጽሑፎችን ባለማግኘታቸው ችግራቸውን ሳይጠቁሙ ያለፉበት ጊዜ አይገኝም ፤ ቢሆንም የታሪክ ሰዎች ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እንብበውና ተመልክተው ያገኙትን ከራሳቸው አስተሳሰብ ጋር በማስማማት እየጻፉ አልፈዋል ።

ይሁን እንጂ የአንዱ ሥነ ጽሑፍ አቀራረብ ከሌላው ጋር ባለመስማማቱ የአንደኛውን አስተሳሰብና አጻጻፍ ሌላው ለማፍረስ የሚሞክርበት ጊዜ አለ ስለዚህ የአንዱን ባለታሪክ አሳብ ብቻ ተመልክቶ ያለ ጥርጥር ስሕተት የሌለበት ፍጹም አድርጎ ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም ።

አባቶች መተርጉማን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲተረጉሙ ሦስት አራት ከዚያም በላይ በሆኑ መንገዶች የትርጓሜ ስልቶችን ማሳየት አቀነባብረው እንደሚናገሩ ሁሉ ታሪክንም መጻፍ ከዚህ አትለፍ ብሎ መንገዱን አጥብቦ ሳይሆን ወደፊት ለሚነሣው አዲስ ትውልድ በሩን ክፍት አድርጎ መተው እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው ብዬ እገምታለሁ ፤ እንግዲህ ስለ ሀገራችን ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ አጀማመር ስጽፍ ከመጻሕፍት አንብቤ ያገኘሁትን ከአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጠይቄ የተረዳሁትን እንጂ እኔ ራሴ በልብ ወለድ ይመስለኛል በማለት ብቻ ለማቅረብ አልሞከርኩም ።

ወደፊት በዕውቀት የተራቀቁ በልዩ ልዩ ቋንቋ የበለጸጉ መጻሕፍትን አንብበውና ተመራምረው አሻሽለው እንዲጽፉ በሩ ሰፊ ነው በሀገራችን በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የተጀመረበትን ዘመን በምንምመለከትበት ጊዜ ሥነ ጽሑፍ ራሱ ከሰው ልጆች የሕይወት ታሪክ ጋር የተጣመረ በመሆኑ ሁኔታውን የምንመለከተው ከታሪክ አንጻር ነው ታሪክ በሥነ ጽሑፍ እንደሚወሰን ሥነ ጽሑፍም የታሪክን አቋም እየመዘገበ በመያዝ ለተተኪ ትውልድ ያስተላልፋል ዛሬ በዓለም ላይ ታሪካቸው ተስፋፍቶ ባህላቸው ዳብሮ የምናያቸው ሕዝቦች ሁሉ አስቀድመው የሥነ ጽሑፍ ባለቤቶች ከመሆናቸው የተነሣ ነው በሀገራችን ግን ከታሪካችን ሥነ ጽሑፋችን ኋላ ቀር በመሆኑ የገዛ ታሪካችንን ለማወቅና ለመረዳት የምንችለው ሌሎች ስለኛ ሀገርና ሕዝብ ባህልና ልማድ ተመራምረው ካሠፈሩት ሥነ ጽሑፍ መሆኑ የማይታበል ትክክለኛ ነገር ነው ።

ቢሆንም ሥነ ጽሑፍ በሀገራችን በኢትዮጵያ ምን ጊዜ እንደተጀመረ ማወቁና ለማወቅ ለሚፈልጉ ታሪክ ተከታታዮች ማቅረቡ እጅግ በጣም አስፈላጊ ሳይሆን አይቀርም ።

ይሁን እንጂ ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ በሀገራችን ምን ጊዜ እንደተጀመረ በምን መለከትበት ጊዜ እግረ መንገዳችንን አንዳንድ የትውልድ ሀረጉችንም እንመለከታለን ።

ከሁለት ሽህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሰባት ዓመተ ዓለም ጀምሮ ከኩሽ ልጅ ከሰብታሕ እስከ ሰባት ሽህ አምስት መቶ አሥር ዓመተ ዓለም እስከ ጲአሪ አንደኛ ድረስ መሆኑ ነው እንጨት ጠርበው ድንጊያ አለዝበው ወርቅ አፍስሰው ጣዖት አቁመው እንደ አሕዛብ ማምለካቸው ባይነገርም እንደሚፈልጉትና እንደሚሰማቸው ልዩ ልዩ አማልክትንና ሟርትንም እያደረጉ ይኖሩ እንደ ነበር ታሪክ ይመሰክራል በዚያም ዘመን በሀገራችን በኢትዮጵያ ጽሕፈት ተጀምሯል ጽሕፈቱ ግን ይጻፍ የነበረው እንደ አሁኑ ጊዜ አጻጻፍ ሳይሆን በሰው በእንስሳት በአራዊት በአዕዋፍና በልዩ ልዩ ቆሳቁሳት እየተቀረጸ ነበር ።

ለምሳሌ በሩን ክፈት ሲል በር ፤ ቢላዋ አምጣ ሲል ቢላዋ ፤ ውሃ ቅዳ ሲል መቅጃውን መጋዝ አምጣ ሲል መጋዙን በጽሑፍ ቀርጾ መላክ የተለመደ ተግባር እንደነበር ይነገራል ይህንን በሰፊው ለመረዳት ቢያስ ፈልግ ሳባ ከተባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅፅ 2 መመልከት ይቻላል ።

ከአዳም ጀምሮ እስከ ፋሌክና እስከ ዮቅጣን ድረስ ሦስት ሽህ አምስት መቶ አሥር ዓመተ ዓለም ዓለሙ ሁሉ አንድ ቋንቋ ይናገር ነበር ዘፍ. 11.1 ነገደ ሴም የሴም ልጆች ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትም ዘመን ይኸው ዘመን ነው ይባላል በኋላ ግን የቋንቋ መለያየት እንደ ተጀመረ በዘፍ. 11 ተጽፎ እናገኛለን ።

ከዚያ በኋላ በፋሌክ ጊዜ የተለያዩ ሰባ ሁለት ቋንቋዎች ተገኝተዋል በዚያን ጊዜ አሥራ አምስት ቋንቋዎች ለሴም ሃያ አምስት ቋንቋዎች ለያፌት ሰላሳ ሁለት ቋንቋዎች ፤ ለካም ስለተሰጡ በየአቅጣጫው ሥነ ጽሑፍ ሊስፋፋ ችሏል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ነገደ ዮቅጣን ለካም ልጅ ለጲአሪ አንደኛ አምስት ዓመታት ለጥ ለበጥ ብለው ከተገዙ በኋላ ራማ የሚባል የሕንድ መሪ በሦስት ሽህ አምስት መቶ ዓመተ ዓለም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጲአሪን ወግቶ እርሱን ገድሎ ሀገሪቱን ያዘ፤በዚያን ጊዜ ሦስቱ ወንድማማቾች ሳባ ፤ አቫልና አፌር እርስ በእርሳቸው ተላልከው በትግራይ ያለውን የሳባን ልጅ አክናሁስ ሰባሁለተኛውን መሪ አድርገው ከሕንድ መሪ ራማ ጋር ተዋጉና እርሱን ድል አድርገው ሀገሪቱን ብሔረ እግአዚት ቋንቋውንም

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# የካህናት ተልእኮ

"ኢህደጋ ለምድር እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም እንበለ ካህናት ወዲያቆናት ፤

እግዚአብሔር ምድርን ያላካህናትና ዲያቆናት ለዘለዓለም አልተዋትም" ይህን ያለው ኢትዮጵያዊው ማኅሌታዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነበር ።

የጎዳር ጽዮን ዋዜማ

ይህ ቃል በእምነት ሲመረመር ምድር ለእግዚአብሔርዘላለማዊት ቤተ መቅደስ መሆንዋንና ይህችም ዘለዓለማዊት ቤተመቅደስ ለዘለዓለሙ ያለ ቅዳሴ እንዳልተተወች የሚያስገነዝብ ነው ፤ እነዚህም ቀዳስያን ካህናት ናቸው ።

ክፍል አንድ

የካህናት ማንነትና ምንነት

ይህ ቃል እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ዘሌዋ 19 ቁ.2 ሲል እግዚአብሔር ለሰዎቹ የተናገረውን ቅዱስ ቃል ለመፈጸምና ለማስፈጸም ከሕዝቡ መካከል ተመርጠው የሚካኑ ሰዎች ናቸው እብ. 5 ቁ.4 ።

እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ በአርአያው የፈጠረው ሰውም ቅዱስ ይሆን ዘንድ በትምህርትና በእምነት ሰውን የሚቀድሱ ካህናት መኖር አስፈላጊ ከሆነ ዘንድ ለዚህ ተልእኮ የተሰሱ ካህናት ይህ ቅዳሴ በሰሞናቸው እንዳይታጉል ተልእኮታቸውን በሚገባ ይፈጽሙ ዘንድ ያስፈልጋል ።

ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው ጊዜና ጊዜው የሚጠይቀው ተልእኮ አይነት የተለየ እንደ መሆኑ መጠን የዘመነ ሐዲስና የዘመነ ብሉይ ካህናት አገልግሎት አይነትም እንዲሁ የብሉይነትና የሐዲስነት ጠባይ አለው ።

ክፍል ሁለት

የብሉይ ኪዳን ካህናት ተልእኮ

በመሠረቱ ከብሉይ ኪዳን ካህናት ይጠበቅ የነበረው ዋና ተልእኮ የኀጢአት ሥርየትና የድኅነት መስዋዕት በማቅረብ ሰውን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ማድረግ ነበር ዘሌዋ.9 ቁ፡1 - 4

በዘመነ ብሉይ ካህናቱ በይበልጥ በዚህ አይነት ተልእኮ ይሰማሩ ነበር በሌላ በኩል የሐዋርያነትንና የሰማእትነትን ተግባር የሚፈጽሙት ግን በይበልጥ ነቢያት ነበሩ ማቴ. 23 ቁ.37 በነቢያትና ካህናት መካከል ያለው ልዩነትና እንደ ሁሉም በሰውና በእግዚአብሔር በሰውና በሰው መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ የሰውን መንፈሳዊና ሥጋዊ ኑሮ በትምርትመ

ለወጥ ሲሆን ተልእኳቸውን የሚፈጽሙት ግን በተለያየ መንገድ ነው ይኸውም ነቢያት በሕዝብ ፊት ለእግዚአብሔር በመቆም ሲሆን ካህናቱ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ለሕዝብ በመቆም ነበር ዘዳ. 18ቁ.18 ዕብ. 8 ቁ1 -5 ።

ሆኖም እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ለሕዝብ የድህነት መሥዋእት ለማቅረብ ሆነ ለመጸለይ ከተሰየሙት ካህናትና መስሎቻቸው መካከል አንዳንዶቹ ተልእኮአቸውን በትክክል ለመፈጸም ተጉ ። ሉቃ. 1ቁ 5 - 14 አንዳንዶቹ ግን የሚሰጡት አገልግሎት በመጥቀም ፈንታ እራሳቸውንም ሆነ ሌላውን የሚጐዱ እንደነበር ታውቋል ምክንያቱም

1ኛ የቃል እንጂ የሥራ ሰዎች ባለመሆናቸው ማቴ. 23ቁ3

2ኛ ውዳሴ ከንቱ የሚያጠቃቸው ግብዞች ስለነበሩ ቁ5

3ኛ በጸሎት ርዝመት እያመካኙ የሃይማኖቶች መበለታትን ቤት የሚበዘብዙ ጨካኞችና የቤተ እግዚአብሔር ቀሳጢዎች በመሆናቸው ቁ.14 ፤

ሀተታ ይህ ድርጊት በአሁኑ ጊዜ እንዳለ ወይም እንደሌለ

4ኛ በሕግ ያለውን ዋና ቁም ነገር ማለት ፍርድን ምህረትንና ታማኝነትን ወደጐን በመተው የግል ጥቅምን ብቻ በማሳደድ ገበያ ጠርገው ከሚያድሩ ምስኪናን ሳይቀር የቅመም አስራት በኩራት በመጠየቅ ሕዝበ እግዚአብሔርን ያሰቃዩ ስለነበር ቁ 23

5ኛ ለመሆን ሳይሆን ለመምሰል የሚጥሩ አፍአውያንና ተመካሕያን ጻድቃን ስለነበሩ ቁ. 25 - 29 ፤ ሉቃ. 18ቁ 11 - 14 ፤

ሀተታ

ሀ ፈሪሳውያን ካህናትና ሌዋውያን ሰዱቃውያን

ለ አስራት በኩራት

ፍርድና ምህረት ታማኝነት ከማንኛውም መልካም ነገር ሁሉ የሚበልጡ የእውነተኛ እምነትና አምልኮተ እግዚአብሔር መለኪያ የሆኑ የቅድስና ተግባሮች ናቸው ሆሴእ.6 ቁ.

6 ፤ በቀና እምነት አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማስፈጸም የካህናት መኖር እንደአስፈለገ ሁሉ የካህናትን ሕይወት ለመጠበቅ ደግሞ የአስራት በኩራት መኖር አስፈልጓል ሆኖም የዘመነ ብሉይ ፈሪሳውያን ካህናት ከማገልገል ይልቅ ለመገልገል በመጣር ፍርድና ምህረት ታማኝነት በጕደለው ጥያቄ አሪታዊው አማኒ የአስራት በኩራት ግዴታቸውን ብቻ እንዲፈጽም በማስገደድ ለግል ጥቅም ተግባር ይተጉ ስለነበር ፤

አለ ጸሁተ ትነጥፋ

ወገመለ ትውህጡ የሚል የዘለፋ ቃል ተነግሮባቸዋል

ተጨማሪ ሀተታ

ብዙዎች የዘመነ ብሉይ ፈሪሳውያን ካህናት ከዚህ አይነቱ ዘለፋ ላይ የወደቁት ከግል ጥቅም ፈላጊነታቸው ብቻ አይደለም በባሕርያዊ ጭካኔም አይደለም ።

1ኛ ዘመኑ እውቀትና ሥልጣኔ የተስፋፋበት ጊዜ ባለመሆኑ በነበራቸው ኦሪታዊት ትምህርትና እውቀት ውዳሴ ከንቱና ትምክህት ያጠቃቸው ነበር ።

2ኛ ሥርአቱ ወንጌላዊ ባለመሆኑ ምህረትና ርሕራሄ አልባ እንዲሆኑ አድርጓቸው ነበር ። ሉቃ. 10ቁ 30 - 38 ።

ከዘመነ ብሉይ ካህናት ይጠበቅ የነበረው ተልእኮና ተልእኳቸውን ባልፈጸሙ ወገኖች ላይ ይነገር የነበረው ዘለፋ ካህናት ከብዙ በጥቂቱ ይህ እስካሁን የታተተው አይነት ነበር ።

ክፍል ሦስት

የሐዲስ ኪዳን ተልእኮ

የዘመነ ሐዲስ የመጀመሪያ የክርስቶስ ልደት ስለሆነ መስዋእተ ኦሪትን ሽሮ መስዋእተ ሐዲስን በመተካት የመጀመሪያው ሊቀ ካህናት ሆኖ በራሱ መስዋእትነት ለሰው ዘር ሁሉ አስፈላጊ የሆነውን የድህነት ዓለም ተልእኮ የፈጸመው እራሱ ክርስቶስ ነው ።

የሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት የሆነው መድኃኒታችን ክርስቶስ በሌሎች ሊፈጸም የማይችለውን የድኅነተ ዓለም ተልእኮ በራሱ ሊቀ ካህናትነት ከፈጸመ በኋላ ዓለምን ያለ ካህናት አልተወም ስለዚህ የእርሱን አርአያ ተከትለው ዓለምን የሚቀድሱ ካህናትን እስከ ፍጻሜ ድረስ ለማስነሳት ባለው መለኮታዊ ፕላን መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማያዊ ኃይልን የታጠቁ አስራ ሁለት ሐዋርያት መረጠ ። ማቴ . 10ቁ1 የዘመነ ብሉይ ካህናት ተልእኮ በአማኝነትና በሥብ አሜሽነት ተግባር የተወሰነ ነበር ። የሐዲስ ኪዳን ካሕናት ተልእኮ ግን ከዚህ የላቀና የሰፋ በመሆኑ ክርስቶስ ሐዋርያትን እራሱ አስተምሮ ከና ህዝብን እንዲያገለግሉ ወደ ህዝብ የላካቸው ከዚህ የበለጠ አገልግሎት እንዲያበረክቱ በማስጠንቀቅ ነበር ። ማቴ. 5ቁ.20 ።

1ኛ በሰውና በእግዚአብሔር

2ኛ በሰውና በሰው መካከልም ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ነው ።

ክፍል አራት

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መልካም ግንኙነት ይኖር ዘንድ ሊደረግ የሚገባው ተልእኮ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የአባትነትና ልጅነት ጠባይ ያለው ግንኙነት ለመፍጠርና የተፈጠረውንም ግንኙነት በጥንቃቄ ለመጠበቅ ማንኛውንም አገልግሎት ለመፈጸም የካህናት ድርሻ ነው ይህም ተልእኮ ፤



www.ethiopianorthodox.org

ሀ. ያላመኑትን ማስተማር ማሳመን ማጥመቅ ማቅረብ ወዘተ... ማቴ. 23 ቁ. 20 ፤ ሮሜ 10. ቁ 10 - 27 ።

ለ. ያመኑትንና የጸኑትን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዳያቋርጡና ተመልሰው ወደ ኀሀነም እንዳይሆኑ መጠበቅ ማጽናናት ማጠናከር ወዘተ ... 2 ጴጥ 10 ቁ. 14 - 20

ይህንንም ለማድረግ ካህናት ዘወትር የናላ ዊነት ተልእኳቸውን ማጠናከር ይገባቸዋል ሕዝቡ መምህረ ንስሀ እንዲኖረው የተደረገውም በዚሁ ምክንያት ነበር ።

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት የዘለአለማዊ ሕይወት መንገድ ስለሆነ ይህ ጉዳና ጥርጊያ ይሆን ዘንድ ወይም ደግሞ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት የዘለአለማዊ ሕይወት መንገድ ስለሆነ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ይህ ጉዳና ጥርጊያ ይሆን ዘንድ ወይም ደግሞ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት እንደ ግንድና እንደቅርንጫፍ ስለሆነ ቅርንጫፉ ከግንዱ እንዳይለይ ለማድረግ ካህናት የዮሐንስ መጥምቁን ምሳሌነት በመከተል ካህን ፤ ነቢይና ሰማእት ሆኖ ሕዝብን የማገልገል ኃላፊነት አለባቸው ።

## ክፍል አምስት

## በሰውና በሰው መካከል ግንኙነት ይኖር ዘንድ ሊደረግ የሚገባው ተልእኮ

ክርስቶስ አንድ ጊዜ ስለ መንግሥተ ሰማያት ተጠይቆ የሰጠው መልስ መንግሥተ ሰማያት በመካከላችሁ ናት (የሚል ነበር) ሉቃ.17 ቁ. 21

ይህ ቃል ሌላ ከዚህ የላቀ ምስጢር ያለው መሆኑ ቢታወቅም በአንድ በኩል በሰዎች መካከል መልካም ግንኙነት ካለ በምድር ላይ እንደ ገነት መንግሥተ ሰማያት የሚቆጠር ኑሮን ለመኖር እንደሚቻል ይልቁንም ሰው ለሰው በሚያደርገው መልካም ነገር የመንግሥተ ሰማያት ሰው ለመሆን መብቃቱን የሚጠቁም ነው ይህ ከሆነ ዘንድ በሰውና በሰው መካከል ሰላምና ፍቅር የሰፈነበት መልካም ግንኙነት ይኖር ዘንድ በማስተማር ሁሉም በዚህ አረቦናዊ ግንኙነት መንግሥተ ሰማያት እንዲኖር ማድረግ ካህናት ከተካኑበትና በመልካም ተልእኳቸው አማልክት ዘበምድር ከሚሰኙበት ዓቢይ የሥራ ክፍል አንዱ ስለሆነ ፍትሕ ምሕረትና ታማኝነት ባለው ሁኔታ ተልእኳቸውን መፈጸም ይገባቸዋል ። በሰውና በሰው መካከል ያለው ግንኙነት በፍቅርና በወንድማማችነት ቅድስና ለማከበር የሚፈጽሙትንም ተልእኮ በሚከተለው አይነት መመሪያ መፈጸም ይኖርባቸዋል ።

1ኛ ማንኛውም ሰው ለራሱ ሊደረግለት የሚገባውን እሱም ለሌላው እንዲያደርግ በራሱ ላይም ሊደረግበት የማይፈቅደውን ግን እርሱም በሌላው ላይ እንዳያደርግ ማስተማር ይህም በቃል ብቻ ሳይሆን በግብርም ጭምር ማቴ. 6 ቁ. 12 ።

2ኛ የሰው ልጅ የሚያየውን ወንድሙን ሳይወድ የማያየውን እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለት ስለማይቻል እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙንም እንዲሁ እንዲወድ በማድረግ የተቀደሰ ማኅበራዊ ኑሮ በሰዎች መካከል እንዲሰፍን መጣር 1 ዮሐ. 4 ቁ. 20 ።

በሰውና በእግዚአብሔር

በሰውና በእግዚአብሔር በሰውና ሰው መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ የማንኛው ም ተልእኮ ፍጻሜ ስለሆነ የዘመን ሐዲስ ካህናት ይህንተልእኮ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የዘወትር ሰሞነኞች ናቸው ።

## ክፍል ስድስት

## የዘመኑ ካህናት የዘመኑን ሕዝብ ለማገልገልና ለመገልገል የሚያስፈልጋቸው ዝግጅት

ሀ. ለማገልገል የዘመኑን ሕዝብ ለማገልገል የሚሰየሙ ካህናት የሚያገለግሉት ሕዝብ ፍላጐት በበለጠ ለማርካት ይችሉ ዘንድ በይበልጥም የሚከተሉትን ግዴታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል ።

1ኛ ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም የሚለውን ጥንታዊና ዘመናዊ መፈክር በግብር መተርጐም ።

2ኛ አላማን ማወቅ

3ኛ አላማን መጠበቅ

4ኛ ብርሃን ወንጌል ከእንቅብ በታች ሳይጣል በመቅረዝ ላይ እንዲያበራ ማድረግ ማለት ... የስብከተ ወንጌል ሥራ በግል ጥቅም ሩጫ ግርዶሽ ሥር እንዳይወድቅ ።

5ኛ ለሥራው ቀናኢነት ያለው መሆን

6ኛ ያሉበትን ጊዜና የጊዜ ግዴታ ማወቅ ማለት - በማያውቁት ዓለም መኖር የሚሰጠውም ትምህርት ለጊዜው በሽታ አብነትነት የሌለው መድኃኒት እንዳይሆን ያለፉትንና የተማሩትን አዳምና ሔዋን ዘወትር ከመተቸት ይልቅ የዘመኑን አዳምና ሔዋን ከስሕተት ለመጠበቅ እንዲቻል ።

7ኛ ከቃል ስብከት ይልቅ የክርስቶስ ሕይወትን አስፈላጊነት በተግባርና በራስ የፍቅርና የደስታ ኑሮ ምሳሌነት ማስተማር ።

በሚለዋወጥ አለም ላይ የማይለወጠውን ቃለ እግዚአብሔር በዘመኑ ቋንቋና አቀራረብ በመስበክ ለዘመኑ ሕዝብ ጆሮ ተሰሚነት ያለው እንዲሆን ማድረግ ።

ለ. ለመገልገል

ሕዝብን የሚያገለግሉ ካህናት በአጸፋው ለመገልገል ይችሉ ዘንድ በቅድሚያ ምእመናንን በሰበካ ጉባኤ ማስተባበርና ማደራጀት ይኖርባቸዋል ። ዋናው ተልእኳቸው ሰውን በትክክለኛ እምነትና ምግባር መቀደስ ፤ በጥምቀትና ቁርባን ማደስ መሆኑ በምእመናን ዘንድ የጐላ የተረዳ ስለሆነ በአገለገሉ መጠን መገልገል እንዳለባቸው ሕዝበ ክርስቲያኑ ያምናል ።

የየሰበካው ምእመን በሰበካ ጉባኤ ከተደራጀም ይህን ለማድረግ የፈቃድና የገንዘብ ድህ አይደለም በዚህ አይነት ምእመናኖቻቸውን ያደራጁ የምሥራቅና ምእራብ ካህናት ከራሳቸው አልፈው ተርፈው የሌላውን ችግር ማቃለል እጃቸውን እስከ ባሕር ማዶ ከሚዘረጉበት ደረጃ ደርሰዋል ።የእኛም ቤተ ክርስቲያን በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝበ ክርስቲያን ያላት እንደመሆኗ መጠን ምእመናቿን በሰበካ ጉባኤ ካደራጀች በአንድ በኩል በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ኢትዮጵያ ልመናንና ድሕነትን ለማጥፋት ለምታደርገው ዘመቻም ፍጹም ተባባሪ እንደመሆን ያስቆጥራታል ።

ምእመናን ካህናቶቻቸውን ለማገልገል የሚችሉትም በበጐ ፈቃድ በሚሰጥ አስራት ወይም ልዩ ልዩ የወርና የአመት አስተዋጽኦና ስጦታ ነው ።

ካህናት ሕዝብን ለማገልገል የታመኑ ከሆኑ ምእመናንንም እነሱን ለማገልገል የታመኑ እንደሆኑ አያጠራጥርም ።

የግል ጥቅምን የወገንና የፍቅረ ንዋይን የስስትንና ትዕቢትን ፊተኛ ድል ነስተው ሕዝብን በማገልገል ክርስቶስን ለሚከተሉ እጽፍ ድርብ እኅት ወንድም እናትና አባት ዘመድ አዝማድ ይኖራቸዋል ።

የማይሠራ አይብላ የሚለውን ቃለ መጽሐፍና ራት የሌለው ቄስ እንደልብ አይቀድስ የሚለውን ቃለ አበው በማገናዘብ ለመገልገል ብቻ ሳይሆን ለማገልገል ቀሰው በአንብሮተ እድ ብቻ ሳይሆን በአንብሮተ ትምህርትም ተክነው ሕዝብን በወንጌል ትምህርትና እውቀት በእምነትና ምግባር የሚቀድሱ እንዲሁም የአገልግሎት ዋጋቸውን ለንደአራቱ ምሕረትና ታማኝነት በሌለው መንገድ ሳይሆን በሕገ ወንጌል የሚጠየቁ ካህናት በእርግጥ ቅዳሴያቸው ያርጋል ። ይረግ ፤ ተልእኳቸው ይሠምራል ፤ ይሥመር ፤ እንደገብር ሃካይ ሳይሆን እንደገብር ሄር በጥቂቱ የታመኑ ብልሆች በብዙ ይሾማሉ ፤ ይሾሙ ወደ ጌታቸውም ደስታ ይገባሉ ፤ ይግቡ ፤

መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

# ሥነ ጽሑፍ...

ከገጽ ፳ የዞረ

ግዕዝ አሉት ፤ ከዚያ ዘመን እንሥቶ እስከ ንግሥተ ሳባ ድረስ አራት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ይሆናል ሥነ ጽሑፍም በዚሁ ዘመን በግእዝ ቋንቋ እጅግ በጣም የተስፋፋ መሆኑን ታሪክ በሰፊው ያስረዳናል ።

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት በሀገራችን በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የተጀመረው በሁለት ሽህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሰባት ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ በፊት መሆኑ ነው ጀማሪዎችም የኩሽ ልጆች ካማውያን ናቸው ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ



# የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

የማርቆስ ወንጌል ። ምዕራፍ ፬

በዕንቅብ ሥር ያለ መብራት

፳፩እንዲሁም አላቸው ፦ መብራትን ከዕንቅብ ወይም ከአልጋ በታች ሊያኖሩት ያመጡታልን ? በመቅረዝ ላይ ሊያኖሩት አይደለምን ? ፳፪እንዲገለጥ ባይሆን የተሰወረ የለምና ፤ ወደ ግልጥ እንዲመጣ እንጂ የተሸሸገ የለም ። ፳፫የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ ። ፳፬አላቸውም ፦ ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ ። በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል ። ፳፭ላለው ይሰጠዋልና ፤ ከሌለውም ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል ።

የሚያድገው ዘር ምሳሌ

፳፮እርሱም አለ ፦ በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት ፤ ፳፯ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም ፤ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል ። ፳፰ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች ። ፳፱ፍሬ ግን ሲበስል መከር ደርሶአልና ወዲያው ማጭድ ይልካል ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
ፖስታ ሣጥን ቁጥር 30755
አዲስ አበባ ።



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኲ | ኳ | ኴ | ኵ |
| ጐ | ጒ | ጓ | ጔ | ጕ |
| ቈ | ቊ | ቋ | ቌ | ቍ |
| ኈ | ኊ | ኋ | ኌ | ኍ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሏ | ሟ | ሯ | ሷ | ሿ | ቧ | ቷ |
| ቿ | ኗ | ኟ | ዟ | ዧ | ዷ | ጧ |
| ጯ | ጿ | ፏ | | | | |

# ሀ ✝ ሁ

መልእክተ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወልደ ፡ ዘብዴዎስ ፡ ቀዳማዊ ። ንዜንወክሙ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘሀሎ ፡ እምትካት ፡ ውእቱ ፡ ዘሰማዕናሁ ፡ በእዘኒነ ፡ ውእቱ ፡ ወዘርኢናሁ ፡ በአዕይንቲነ ፡ ውእቱ ፡ ወዘጠየቅናሁ ፡ ወዘገሰሳሁ ፡ እደዊነ ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ። እስመ ፡ ሕይወት ፡ ተዐውቀት ፡ ለነ ፡ ወርኢናሃ ፡ ወስምዐ ፡ ኮነ ፡ ወንዜንወክሙ ፡ ንሕነ ፡ ሕይወተ ፡ እንተ ፡ ለዓለም ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ወተዐውቀት ፡ ለነ ። ወርኢናሃ ፡ ወሰማዕናሃ ፡ ወንዜንወክሙ ፡ ለክሙኒ ፡ ከመ ፡ አንትሙኒ ፡ ትኩኑ ፡ ሱታፌ ፡ ምስሌነ ፡ ወሱታፌነሰ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወምስለ ፡ ወልዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ወዘንተ ፡ ንጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ ትፍሥሕትክሙ ፡ ፍጽምተ ፡ ትኩን ፡ ብክሙ ። ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ዜና ፡ እንተ ፡ ሰማዕናሃ ፡ እምኔሁ ፡ ወንዜንወክሙ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ፡ ወጽልመትሰ ፡ አልቦ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢአሐቲ ። ወእመሰ ፡ ንቤለክሙ ፡ ብነ ፡ ሱታፌ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ነሐውር ፡ ንሔሱ ፡ ወኢንገብራ ፡ ለጽድቅ ፡ ወለርትዕ ። ወእመሰ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ነሐውር ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃን ፡ ሱቱፋን ፡ ንሕነ ፡ በበይናቲነ ፡ ወደሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያነጽሐነ ፡ እምኵሉ ፡ ኀጣውኢነ ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ኄ | ሞ | ዞ |
| በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ዥ |
| ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ዧ | ሖ |
| ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ዤ | ሕ | ጦ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ዣ | ሔ | ፐ | ጮ |
| ወ | ዙ | ዢ | ሓ | ጤ | ዌ | ዮ |
| ዘ | ዡ | ሒ | ጣ | ጨ | ይ | ኮ |
| ዠ | ሑ | ጢ | ጫ | ዬ | ከ | ኾ |
| ሐ | ጡ | ጪ | ያ | ኬ | ኸ | ሎ |
| ጠ | ጩ | ዪ | ካ | ኼ | ል | ሞ |
| ጨ | ዩ | ኪ | ኻ | ሌ | ም | ና |
| የ | ኩ | ኺ | ላ | ሜ | ን | ኛ |
| ከ | ኹ | ሊ | ማ | ኔ | ኝ | ሶ |
| ኸ | ሉ | ሚ | ና | ኜ | ስ | ሾ |
| ለ | ሙ | ኒ | ኛ | ሴ | ሽ | ዖ |
| መ | ኑ | ኚ | ሳ | ሼ | ዕ | ፎ |
| ነ | ኙ | ሲ | ሻ | ዔ | ፍ | ጾ |
| ኘ | ሱ | ሺ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |
| ሰ | ሹ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ሸ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሦ |
| ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ሥ | ቶ |
| ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሤ | ት | ቾ |
| ጸ | ቁ | ሪ | ሣ | ቴ | ች | ኆ |
| ቀ | ሩ | ሢ | ታ | ቼ | ኅ | ጶ |
| ረ | ሡ | ቲ | ቻ | ኄ | ጵ | ዖ |
| ሠ | ቱ | ቺ | ኃ | ጴ | ፅ | ፖ |
| ተ | ቹ | ኂ | ጳ | ፄ | ፕ | ጆ |
| ቸ | ኁ | ጲ | ፃ | ፔ | ጅ | አ |
| ኀ | ጱ | ፂ | ፓ | ጄ | እ | ቦ |
| ጰ | ፁ | ፒ | ጃ | ኤ | ብ | ጎ |
| ፀ | ፑ | ጂ | ኣ | ቤ | ግ | ዶ |
| ፐ | ጁ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| ጀ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፻ | |
| 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 | |

፲፻ 1000 ፼ 10.000

ኤ ቢ ሲ ዲ ኢ ኤፍ ጂ ኤች አይ ጄ ኬ ኤል ኤም ኤን
a b c d e f g h i j k l m n
ኦ ፒ ኪው ኦር ኤስ ቲ ዩ ቪ ደብሊው ኤክስ ዋይ ዜድ
o p q r s t u v w x y z

ABCDEFGHIJKLMN
OPQRSTUVWXYZ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸሎትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org